በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት

በመንግስት ግዥና ንብረት ማስወገድ አገልግሎት

በጋራ የሚፈለጉ ተመሳሳይ ዕቃዎችና አገልግሎቶች የማዕቀፍ ስምምነት ግዥ አፈፃፀም እና ውጤታማነትን በተመለከተ የተከናወነ የክትትል ኦዲት ሪፖርት

የካቲት 2011 ዓ.ም

አዲስ አበባ

ማ ው ጫ

የዋና ዋና ግኝቶች ማጠቃለያ (ድርሞ)........ I

ክፍል አንድ........ 1

መግቢያ........ 1

የክትትል ኦዲቱ ዓላማ........ 2

የክትትል ኦዲቱ ወሰንና ዘዴ........ 2

የክትትል ኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች........ 3

ክፍል ሁለት........ 4

የኦዲት ግኝቶች........ 4

አገልግሎቱ በደንቡ የተሰጠውን ተግባርና ኃላፊነት ለመወጣት እና ዓላማውን ለማስፈፀም ያለው የሰው ኃይልና ድርጅታዊ አቅምን በተመለከተ፤........ 4

የአገልግሎቱ የግዥ ተግባር በአዋጁና አዋጁን ለማስፈፀም በወጡ ደንቦችና መመሪያዎች መሰረት መፈጸሙን በተመለከተ፡-........ 5

አገልግሎቱ የባለበጀት መ/ቤቶችን የግዥ ፍላጎት ማሰባሰብ፣ መለየትና ማደራጀትን በተመለከተ፤........ 9

አገልግሎቱ ባዘጋጀው ስትራቴጅክ ዕቅድ መሠረት ዓመታዊ የግዥ ዕቅድ ማዘጋጀቱን፣ ዕቅዱን ተግባራዊ ማድረጉን እንዲሁም የዕቅድ ክንውን ሪፖርት ማቅረቡን በተመለከተ፤........ 12

የመንግስት መ/ቤቶች የሚጠቀሙባቸውን ተመሳሳይ ዕቃዎችና አገልግሎቶች ዝርዝር ተጠንቶ የግዥ አገልግሎት ስለመከናወኑ፤........ 15

አገልግሎቱ በሚፈለገው ጊዜና መጠን በጋራ የሚፈለጉ ዕቃዎችና አገልግሎቶች ግዥ በማከናወን ለተጠቃሚዎች ማድረስን በተመለከተ፤........ 16

የመንግሥት ግዥና ንብረት ማስገወድ አገልግሎት የግዥ ሂደት ከመንግስት መ/ቤቶች የበጀት አመት /ፕሮግራም/ ጋር የተጣጣመ መሆኑን በተመለከተ፤........ 19

አገልግሎቱ የጨረታ ሠነድ ሥራ ላይ ከመዋሉ በፊት በግዥ አፅዳቂ ኮሚቴ ተቀባይነት ማግኘቱን ስለማረጋገጡ በተመለከተ፤ 21

አገልግሎቱ የተጫራቾችን ብቃት እና የስራ አፈፃፀማቸውን ማረጋገጡን በተመለከተ፤ 22

አገልግሎቱ በአገር ውስጥ ጨረታ ጊዜ የክፍያ ሁኔታ ስለማመቻቸቱ እና አቤቱታዎችንና ቅሬታዎችን ተቀብሎ የእርምት እርምጃ መውሰዱን በተመለከተ፤ 24

አገልግሎቱ የሚፈራረማቸው የግዥ ውሎች የተሟላ መረጃ /መመሪያ መያዛቸው፣ ተግባራዊ መደረጋቸውን በተመለከተ ስለመከታተሉ እና ለመንግስት መ/ቤቶች በግዥ ዙሪያ ድጋፍ ስለማድረጉ፤ 26

አገልግሎቱ የሚፈራረማቸው የግዥ ውሎች የቴክኒክ ፍላጎት መግለጫ /Specification/ የያዙ መሆናቸውን እና በዛ መሰረት ግዥ መፈፀሙን በተመለከተ፤ 27

አገልግሎቱ የሚፈራረመው የግዥ ውል የገበያ ጥናትና መረጃን የተመረኮዘ መሆኑን 30

አገልግሎቱ በጨረታ ሰነዱ ላይ ስለማስረከቢያ ቦታ፣ ጊዜ እንዲሁም የዋጋ ማስተካከያ ስለሚደረግበት ሁኔታ ያካተተ መሆኑን በተመለከተ፤ 33

አገልግሎቱ ጥራታቸውን የጠበቁ ዕቃዎች በተመጣጣኝ ዋጋ መግዛቱን እና ጥቅል ግዥ በመፈፀም ኢኮኖሚያዊ ጥቅም ማስገኘቱን በተመለከተ፤ 34

አገልግሎቱ ከሌሎች አካላት ጋር የመረጃ ልውውጥ ስርዓት ስለመዘርጋቱ እና ግንዛቤ መፍጠሩን በተመለከተ፤ 36

አገልግሎቱ የምክርና ስልጠና አገልግሎት ስለመስጠቱና እና የመወያያ መድረኮችን ማዘጋጀቱን በተመለከተ፤ 38

ክፍል ሦስት 41

የመደምደሚያ ሀሳብ (Conclusion) 41

3.1. እርምጃ የተወሰደባቸውና መሻሻል የታየባቸው 41

3.2. እርምጃ ያልተወሰደባቸው እና መሻሻል ያልታየባቸው 43

ክፍል አራት 46

የማሻሻያ ሀሳቦች (Recommendation) 46

የዋና ዋና ግኝቶች ማጠቃለያ (ድርሞ)

(Executive summary)

የክትትል ኦዲቱ ዓላማ የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት በ2005/2006 ዓ.ም በመንግስት ግዥና ንብረት ማስወገድ አገልግሎት በጋራ የሚፈለጉ ተመሳሳይ ዕቃዎችና አገልግሎቶች የማዕቀፍ ስምምነት ግዥ አፈፃፀምና ውጤታማነትን በተመለከተ ባካሄደው የክዋኔ ኦዲት መሰረት በተገኙ ግኝቶች ላይ የተሰጡትን የማሻሻያ ሀሳቦች ተግባራዊ ለማድረግ አገልግሎቱ በደብዳቤ ቁጥር ግንማ 4/1/12/8265 ጥር 18 ቀን 2007 ዓ.ም. ለመ/ቤታችን ባቀረበው የድርጊት መርሀ-ግብር መሰረት የተወሰዱ የማስተካከያ እርምጃዎች መኖራቸውን ለማረጋገጥ ሲሆን፣ እስካሁን ያልተቀረፉ ችግሮች ካሉ ምክንያቱን በመለየትና በማጣራት ችግሮቹ እንዲቀረፉ የማሻሻያ ሃሳብ ለመስጠት እንዲሁም የክዋኔ ኦዲቱ ያመጣውን ውጤትና ያስገኘውን ጥቅም ለመገምገም ነው፡፡ በዚህ መሠረት በክትትል ኦዲቱ የተገኙ ዋና ዋና ግኝቶች የሚከተሉት ናቸው፡-

- አገልግሎቱ በደንቡ የተሰጠውን ኃላፊነት ለመወጣት የሚያስችሉ የግዥ ዳይሬክቶሬት እና የውል አስተዳደር ዳይሬክቶሬት በመዋቅሩ መሰረት የሰው ሀይል ያላሟላ መሆኑ፤
- አገልግሎቱ የተሽከርካሪ ግዥን በተመለከተ በራሱ ፍላጎት አሰባስቦ ግዥ የማይፈፅም እና የተሽከርካሪ መለዋወጫዎች፣ የምግብ ጥሬ ዕቃዎች፣ መፅሐፍትና መፅሔቶች ያልገዛ መሆኑ፤
- አገልግሎቱ የህንፃ መሳሪያዎችና የግንባታ ዕቃዎችን በተመለከተ በማእቀፍ ግዥ መፈጸም /መግዛት ሲገባው መመሪያውን በመጣስ በሌሎች ግዢዎች በሚል አካቶ የገዛ መሆኑ፤
- አገልግሎቱ ከ2008-2010 ዓ.ም የውጤት ተኮር ስርዓት የ5 ዓመት ስትራቴጂክ ዕቅድ የትኛው ተግባር በየትኛው ዓመት እንደሚሰራ ተለይቶና በስትራቴጂው የታቀደው ተግባር ከዓመታዊ ዕቅድ ጋር በየዓመቱ በተጣጣመ መልኩ ያልተቀመጠ መሆኑ፤
- አገልግሎቱ የግዥ ሂደቱን በቴክኖሎጂ የመጠቀም የአሰራር ስርዓትና ዘመናዊ የመረጃ አያያዝና ልውውጥ ተግባራዊነት በተጠናከረ መልኩ እየተገበረ አለመሆኑ፤
- አገልግሎቱ የሚያዘጋጀው የግዥ እቅድ ግምታዊ የበጀት መጠን ያላካተተ

እንዲሁም የግዥው አይነት፣ ጨረታ የሚወጣበት ጊዜ፣ ግዥ ተፈፅሞ ርክክብ የሚፈፀምበት ጊዜ በተሟላ ሁኔታ ያላካተተ መሆኑ፣

- አገልግሎቱ ላለፉት ሶስት አመታት (ከ2008-2010 ዓ.ም) ባደረገው የግዥ ሂደት የጨረታ ወቅት የነባር የዕቃና አገልግሎት አቅራቢ ድርጅቶች በድጋሚ ለመወዳደር የበፊት የሥራ አፈጻጸማቸው እንደመስፈርት አለመታየቱ፣
- አገልግሎቱ ከኤጀንሲው በጋራ መጠቀሚያ ዕቃዎች ዝርዝር ያካተታቸው ዕቃዎች (11 ምድብ) የተሰጠ ቢሆንም የሁሉንም ምድቦች ግዥ የማይፈፅም እንዲሁም የፅዳት፣ የጥበቃ፣የጥገና የአገልግሎት ግዥዎችን ያላከናወነ መሆኑ፣
- አገልግሎቱ በሚፈለገው ጊዜና መጠን የጋራ መጠቀሚያ ዕቃዎችና አገልግሎቶችን በተመለከተ ለተጠቃሚ መ/ቤቶች እንዲደርሱ አለማድረጉ፣
- አገልግሎቱ የግዥ ውሉ በስምምነቱ መሰረት ስለመፈጸሙ በመደበኛነት ማለትም በሳምንት ሁለት ጊዜ የሚከታተል ቡድን ያቋቋመው በ2010 ዓ.ም መሆኑና ከዚህ በፊት ለተደረጉት ግዥዎች በውሉ መሰረት ስለመፈፀሙ ክትትል አለማድረጉ፣
- አገልግሎቱ አቅራቢ ድርጅቶች በስምምነቱ መሰረት ተግባራዊ ካላደረጉ የውል ማስከበሪያ ገንዘብ የመውረሻ ስርዓት ቢኖረውም የመንግስት መ/ቤቶች ባለፉት ሶስት ዓመታት በውሉ መሰረት እንዳላስተናገዷቸው የሚገልፁ ቢሆንም አገልግሎቱ ይህንን በማረጋገጥ ገንዘቡን ያልወረሰ መሆኑና ይህን የሚከታተል ቡድን የተቋቋመው በ2010 ዓ.ም መሆኑ፣
- አገልግሎቱ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር የጋራ የስምምነት ሰነድ በመፈራረም ቅንጅታዊ አሰራር ያልዘረጋ መሆኑ፣
- አገልግሎቱ ከዚህ በፊት በኢትዮጵያ ደረጃዎች ኤጀንሲ ደረጃ እንዲወጣላቸው ከተላኩት ዕቃዎች ውስጥ 132ቱ አሁንም ተከታትሎ ደረጃ እንዲወጣላቸው ያላደረገ መሆኑ፣
- አገልግሎቱ ጎማዎችን በሚመለከት በአንበሳ አውቶብስ ድርጅት እንዲፈተሽ የጠየቀበት ሁኔታ ቢኖርም በመፈተሻ ማሽን እጥረት ምክንያት ፍተሻው አለመከናወኑና ይህን ፍተሻ ለማከናወን ሌላ አማራጭ ያልተጠቀመ መሆኑ፣ እንዲሁም በኢትዮጵያ የተስማሚነት ምዘና ድርጅት በመፈተሻ መሳሪያ እጥረት ምክንያት መፈተሽ ያልተቻሉትን እቃዎች እንደ ቶነር ካርትሬጅና የመሳሰሉትን እቃዎች በሌሎች አካላት መፈተሽ የሚቻልበትን ሁኔታ አለማመቻቸቱ፣

- የገበያ ጥናት የሚሰራ ቡድን በማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ኤጀንሲ የተቋቋመው በ2010 ዓ.ም. መሆኑና አገልግሎቱ ከ2008-2010 ዓ.ም ለገዛቸው እቃዎች በማዕከላዊ ስታትስቲክስ ኤጀንሲ የዕቃዎች የጅምላ ዋጋ ያልተጠና እንዲሁም የዋጋ ማሻሻያው በችርቻሮ ዋጋ መሆኑ፤
- አገልግሎቱ በየበጀት ዓመቱ በመ/ቤቶች ለሚፈለጉ የጋራ መጠቀሚያ ዕቃዎችና አገልግሎቶች የግዥ ገንዘብ ግምታዊ በጀት የሚመለከተውን አካል የማይጠይቅ መሆኑና ለግዥው የተመደበው በጀት እና የግዥው መጠን መመጣጠኑን በማያረጋግጥ ማስተካከያዎችን የማያደርግ መሆኑ፤
- አገልግሎቱ የራሱን የመረጃ ቋት/ዳታቤዝ/ ከማደራጀት ባለፈ በቴክኖሎጂ የተደገፈ የመረጃ ልውውጥን ተግባራዊ ያላደረገ መሆኑ፤
- አገልግሎቱ በመንግስት መ/ቤቶች ተመሳሳይ በጋራ የሚፈለጉ ዕቃዎችና አገልግሎቶች ጥቅል ግዢ መፈፀም ያስገኘውን ኢኮኖሚያዊ ጥቅም በተመለከተ የፋይዳ ጥናት አከናውኖ የማያውቅ መሆኑ፣
- አገልግሎቱ በግዥ አፈፃፀም ዙሪያ በእቅድ ይዞ የሰጠው ስልጠና አለመኖሩ፣

ክፍል አንድ

መግቢያ

1. መንግሥት በየዓመቱ ከሚመድበው በጀት ውስጥ እስከ 70 በመቶ የሚደርሰው ለግዥ የሚውል ነው፡፡ የግዥ አፈፃፀም ውጤታማነት የሚለካው ፍላጎትን ለማሟላት ወጪ ለተደረገ ገንዘብ ተገቢውን ጥቅም ማስገኘት መቻሉ ሲረጋገጥ ነው፡፡ ይሁን እንጂ እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ ከፍተኛ መጠን ያለው የመንግሥት ሀብት የሚፈስበት የመንግሥት ግዥ ተገቢውን ትኩረት ባለማግኘቱ አፈፃፀሙ አዝጋሚና ለብክነት የተጋለጠ ነበር፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ለግዥ ሥራ የሚመደቡ ባለሙያዎችም በቂ የትምህርት ዝግጅት የሌላቸውና በልምድ ብቻ የሚሠሩ ነበሩ፤

2. ንብረት ማስወገድንም በተመለከተ ጥቅም ላይ የማይውል የመንግሥት ንብረት በተገቢው ጊዜ የማስወገድ ባህል በአገራችን የተለመደ አልነበረም፡፡ በዚሁ ምክንያት በመንግሥት መ/ቤቶች ይዞታ ሥር የሚገኙ ንብረቶች ለአገልግሎት በማይፈለጉበት ጊዜ በወቅቱ ስለማይወገዱ ለዝናብና ፀሐይ ተጋልጠው በሚደርስባቸው እንግልት ዋጋቸው እየቀነሰ መንግሥት ከንብረቶቹ ሊያገኝ የሚገባውን ጥቅም የሚያጣ ከመሆኑም በላይ ለሌላ አገልግሎት ሊውል የሚገባውን ቦታ ጨምሮ በመያዝ ከፍተኛ ችግር አስከትሏል፡፡

3. ስለሆነም ለመንግሥት ግዥ ለተከፈለ ገንዘብ ተመጣጣኝ ጥቅም መገኘቱን ለማረጋገጥ፣ የግዥ አፈፃፀም እና የንብረት አስተዳደር ሥርዓቱ የበለጠ ሀብትና ጊዜ ቆጣቢ እንዲሁም ግልጽ አሠራርን መሠረት አድርጎ በውድድር ላይ የተመሰረተ እንዲሆን የሚያስችሉ አደረጃጀቶች እንዲኖሩት ማድረግ አስፈላጊ መሆኑ ታምኖበታል፡፡

4. በመሆኑም በመንግሥት ግዥና ንብረት አስተዳደር ረገድ በተደረገው መሠረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ ጥናት የመንግሥት ግዥ አፈፃፀምን ብቃት በከፍተኛ ደረጃ ለማሻሻል ይጠቅማሉ ተብሎ የታመነባቸው የጥናቱ ሀሣቦች የሕግ መሠረት እንዲኖራቸው ለማድረግ ተሻሽሎ በወጣው የመንግሥት ግዥና ንብረት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 649/2001 ከተካተቱ ለውጦች መካከል አንደኛው በመንግሥት መ/ቤቶች በወል የሚፈለጉ እንዲሁም አገራዊ ስትራቴጂካዊ ጠቀሜታ ያላቸውን ዕቃዎችና አገልግሎቶች ግዥ በአንድ ማዕከላዊ ተቋም አማካኝነት አጠቃሎ መግዛት ነው፡፡

5. ይህን ሥራ በኃላፊነት የሚመራ እራሱን የቻለ አካል ማደራጀት ተገቢ መሆኑ ስለታመነበት የመንግሥት ግዥና ንብረት ማስወገድ አገልግሎት በሚል ስያሜ በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 184/2002 ይህ አገልገሎት እንዲቋቋም ተደርጓል፡፡ ስለዚህ ይህን ለፌደራል ባለበጀት መ/ቤቶች፣ ለክልል መንግሥታት፣ ለልማት ድርጅቶችና ለግሉ ዘርፍ ከሚከናወነው ከፍተኛ ግዥ የሚገኘውን ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ለማግኘት እንዲያስችል በጋራ የሚፈለጉ ተመሳሳይ ዕቃዎችና አገልግሎቶች የማዕቀፍ ግዥ እየፈጸመ ይገኛል፡፡

የክትትል ኦዲቱ ዓላማ

6. የክትትል ኦዲቱ ዓላማ የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት በ2005/2006 ዓ.ም በመንግስት ግዥና ንብረት ማስወገድ አገልግሎት በጋራ የሚፈለጉ ተመሳሳይ ዕቃዎችና አገልግሎቶች የማዕቀፍ ስምምነት ግዥ አፈፃፀምና ውጤታማነትን በተመለከተ ባካሄደው የክዋኔ ኦዲት መሰረት በተገኙ ግኝቶች ላይ የተሰጡትን የማሻሻያ ሀሳቦች ተግባራዊ ለማድረግ አገልግሎቱ በደብዳቤ ቁጥር ግንማ4/1/12/8265 ጥር 18 ቀን 2007 ዓ.ም. ለመ/ቤታችን ባቀረበው የድርጊት መርሀ-ግብር መሰረት የተወሰዱ የማስተካከያ እርምጃዎች መኖራቸውን ለማረጋገጥ ሲሆን፣ እስካሁን ያልተቀረፉ ችግሮች ካሉ ምክንያቱን በመለየትና በማጣራት ችግሮቹ እንዲቀረፉ የማሻሻያ ሃሳብ ለመስጠት እንዲሁም የክዋኔ ኦዲቱ ያመጣውን ውጤትና ያስገኘውን ጥቅም ለመገምገም ነው፡፡

የክትትል ኦዲቱ ወሰንና ዘዴ

7. የክትትል ኦዲቱ የሸፈነው በመንግስት ግዥና ንብረት ማስወገድ አገልግሎት በጋራ የሚፈለጉ ተመሳሳይ ዕቃዎችና አገልግሎቶች የማዕቀፍ ስምምነት ግዥ አፈፃፀምና ውጤታማነትን በተመለከተ በተከናወነ የክዋኔ ኦዲት ለተገኙ ግኝቶች/ግድፈቶች/ የተሰጡ የማሻሻያ ሀሳቦችን መሰረት በማድረግ አገልግሎቱ አዘጋጅቶ ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት በላከው የኦዲት ግኝት ማሻሻያ ሃሳቦች የሚተገበሩበት የድርጊት መርሃ ግብር መሰረት ከ2008 ዓ.ም ጀምሮ የክትትል ኦዲቱ እስከተከናወነበት 2010 በጀት ዓመት መጨረሻ ድረስ ባሉት ሶስት በጀት ዓመታት በአገልግሎቱ የተከናወኑ ስራዎችን መሰረት በማድረግ ነው፡፡

8. የክትትል ኦዲቱ በዋነኛነት የተከናወነው በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ የመንግስት ግዥና ንብረት ማስወገድ አገልግሎት እና በክዋኔ ኦዲቱ ወቅት በናሙና ተመርጠው ከታዩ የፌዴራል ባለበጀት መ/ቤቶች መካከል፡- ንግድ

ሚኒስቴር፣ ትምህርት ሚኒስቴር፣ ማዕከላዊ ስታቲስቲክስ፣ የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስጣን፣ የኢትዮጵያ የተስማሚነት ምዘና ድርጅት፣ የኢትዮጵያ የደረጃዎች ኤጀንሲ፣ የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር እና ከከፍተኛ ትምህርት ተቋማት አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ እንዲሁም ከአቅራቢ ድርጅቶች መካከል፡- ኢንተርናሽናል ማርኬተርስ፣ ራዲካል፣ ጁፒተር ትሬዲንግ የክትትል ኦዲት ቡድኑ በአካል በመገኘት ለሚመለከታቸው ሠራተኞችና የሥራ ኃላፊዎች ቃለ-መጠይቅ በማቅረብ እና ለክትትል ኦዲቱ አስፈላጊ የሆኑ ማስረጃዎችን በመከለስና በመተንተን የተካሄደ ነው፡፡

የክትትል ኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች

9. የክትትል ኦዲቱን ለማከናወን እንደመመዘኛ መስፈርት የተመረጡት በክዋኔ ኦዲቱ ወቅት የነበሩ የኦዲት ግኝቶችና የተሰጡ የማሻሻያ ሀሳቦች እንዲሁም አገልግሎቱ በኦዲት ግኝቱ ላይ የእርምት እርምጃ ለመውሰድ ያዘጋጀው የድርጊት መርሃ ግብር ናቸው፡፡

ክፍል ሁለት

የኦዲት ግኝቶች

አገልግሎቱ በደንቡ የተሰጠውን ተግባርና ኃላፊነት ለመወጣት እና ዓላማውን ለማስፈፀም ያለው የሰው ኃይልና ድርጅታዊ አቅምን በተመለከተ፤

10. በክዋኔ ኦዲቱ ወቅት የተገኘው፤

11. አገልግሎቱ የተሰጠውን ኃላፊነት ለመወጣት የሚያስችሉ የግዥ እና የውል አስተዳደር የስራ ሂደት በመዋቅሩ ከተፈቀደለት 56 የሰው ኃይል ውስጥ እስከ ሰኔ 30/2005 ዓ.ም በ30 (54%) የሥራ መደቦች ላይ ሰው ያልተመደበባቸው ሲሆን፣ በአጠቃላይ ለአገልግሎቱ ከተፈቀደው 234 የሰው ኃይል ውስጥ እስከ ሰኔ 30/2005 ዓ.ም. 127ቱ (54 በመቶ) የሰው ኃይል ሳይቀጠርባቸው ክፍት እንደሆኑ፣

12. በአገልግሎቱ የግዥ አፈፃፀም ሂደቱን(ከጨረታ ሰነድ ጀምሮ ዕቃው ገቢ እስከሆነበት ድረስ) የሚያሳዩ የግዥ ሰነዶችና ማስረጃዎች የሚይዝ ራሱን የቻለ ባለሙያ አለመመደቡና የግዥ ማስረጃዎችም በተደራጀ ሁኔታ ያልተቀመጡ መሆኑ ተገኝቶ ነበር፡፡

13. የመንግስት ግዥና ንብረት ማስወገድ አገልግሎት በደንቡ የተሰጠውን ኃላፊነት ቀልጣፋና ውጤታማ በሆነ መልኩ ተግባራዊ ለማድረግና ዓላማውን ለማስፈፀም የሚያስችል በመዋቅሩ መሰረት የተሟላ የሰው ኃይል አደረጃጀትና ግብዓት ሊኖረው እንደሚገባ የማሻሻያ ሀሳብ ተሰጥቶ ነበር፡፡

14. የመንግስት ግዥና ንብረት ማስወገድ አገልግሎት ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት በደብዳቤ ቁጥር ግንማ 14/1/12/8265 ጥር 18 ቀን 2007 ዓ.ም አዘጋጅቶ በላከው የድርጊት መርሃ-ግብር ለግዥና ለውል አስተዳደር የስራ ሂደት የተፈቀደ የስራ መደብ 56 ቢሆንም እስከ ታህሳስ 23 2007 ዓ.ም በሰው ሀይል የተሟላው መደብ 34 ብቻ መሆኑን እና ሌሎቹን መደቦች ማሟላት ያልተቻለው እስከ 2005 በጀት ዓመት በአገልግሎቱ የሚገዛው ዕቃ መጠን አነስተኛ በመሆኑና ከ2006 በጀት ዓመት በኋላ ደግሞ በቢሮ እጥረት ምክንያት እንደሆነና ችግሩ እንደተፈታ፣ በቀጣይ ሌሎቹን የአገልግሎቱን መደቦች እንደሚያሟላ ገልጿል፡፡

15. የክትትል ኦዲት በተከናወነበት ወቅት የሚከተሉት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡-

16. አገልግሎቱ የተሰጠውን ኃላፊነት ለመወጣት የሚያስችሉ የግዥ ዳይሬክቶሬት እና የውል አስተዳደር ዳይሬክቶሬት በመዋቅሩ ከተፈቀደላቸው 107 የሰው ኃይል ውስጥ እስከ ግንቦት ወር 2010 ዓ.ም 69 (64.5%) በሥራ መደቡ ላይ ሰው ያልተመደበባቸው መሆኑን፣ በአጠቃላይ ለአገልግሎቱ ከተፈቀደው 325 የሰው ኃይል ውስጥ እስከ ግንቦት ወር 2010 ዓ.ም. 151ዱ (46.5 በመቶ) ሰው ሳይቀጠርባቸው ክፍት መሆኑን በክትትል ኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎች ለማወቅ ተችሏል፡፡

17. የአገልግሎቱ የበላይ ሃላፊዎች ስለጉዳዩ ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ አገልግሎቱ ካለበት የቢሮ እጥረትና የደመወዝ ስኬል ዝቅተኛ መሆን የተነሳ የተሰጠውን ኃላፊነት ለመወጣት የሚያስችሉ የሚያስችል በመዋቅሩ መሰረት የተሟላ የሰው ኃይል አደረጃጀትና ግብዓት ያልተሟላ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

18. ይሁን እንጂ አገልግሎቱ በአዋጅ የተሰጠውን ስልጣንና ተግባር ለመፈፀምና ከአገልግሎቱ ሊገኝ የሚችለውን ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ በቅልጥፍናና ውጤታማ በሆነ አሰራር ለማግኘት እንዲቻል በተሟላ የሰው ኃይልና ድርጅታዊ አቅም ካልጎለበተ በስተቀር የተቋቋመበት አላማ ሊሳካ የማይችል መሆኑ ሊታወቅ ይገባል፡፡

የአገልግሎቱ የግዥ ተግባር በአዋጁና አዋጁን ለማስፈፀም በወጡ ደንቦችና <u>መመሪያዎች መሰረት መፈጸሙን በተመለከተ፡-</u>

19. በክዋኔ ኦዲቱ ወቅት የተገኘው፤

20. የመንግስት ግዥና ንብረት ማስወገድ አገልግሎት የተሽከርካሪ እና የመድህን አገልግሎት ግዥ ፍላጎት አሰባስቦ በወጣው ደንብና መመሪያ መሰረት የማዕቀፍ ስምምነት ተፈራርሞ በራሱ ዕቅድ መሰረት ግዥ የማይፈፅምና ከገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ትብብር ሚኒስቴር ትዕዛዝ ሲመጣለት ብቻ ግዥ የሚፈፅም መሆኑ፣

21. የተሽከርካሪ መለዋወጫዎች፣ የምግብ ጥሬ ዕቃዎች፣ የደንብ ልብሶች፣ የኤሌትሪክ ዕቃዎችና መሳሪያዎች፣ መፅሐፍትና መፅሔቶች እና የህንፃ መሳሪያዎችና የግንባታ ዕቃዎችን ግዥ ለመንግስት መ/ቤቶች ያልፈጸመ መሆኑ ፣

22. የመንግሥት መ/ቤቶች ከፌዴራል መንግስት የክፍያ መመሪያ ቁጥር 4/2003 እና ከግዥ አፈፃፀም መመሪያ ውጭ ክፍያ ፈፅመው ዕቃ እንዲረከቡ በአገልግሎቱ በታዘዙት መሰረት መ/ቤቶቹ ለሚገዙት ዕቃ ከመረከባቸው በፊት ቅድመ ክፍያ

እንዲፈጽሙ መደረጋቸው እና የቅድመ ክፍያ እንዲፈፅሙ ሲደረግም የዕቃ አቅራቢዎች ከሚወስዱት የገንዘብ መጠን ጋር ለመንግስት መ/ቤቶቹ እኩል የሆነ ዋስትና እንዳላቀረቡ ተገኝቶ ነበር፡፡

23. የመንግስት ግዥና ንብረት ማስወገድ አገልግሎት በጋራ ለሚፈለጉ ተመሳሳይ ዕቃዎችና አገልግሎቶች የግዥ ተግባር ተጠያቂነትን ከማጠናከር አንፃር በአዋጁና አዋጅን ለማስፈፀም በወጡ ደንቦችና መመሪያዎች መሰረት መፈፀሙን ማረጋገጥ አለበት የሚል የማሻሻያ ሀሳብ ተሰጥቶ ነበር፡፡

24. የመንግስት ግዥና ንብረት ማስወገድ አገልግሎት ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት በደብዳቤ ቁጥር ግንማ 14/1/12/8265 ጥር 18 ቀን 2007 ዓ.ም አዘጋጅቶ በላከው የድርጊት መርሃ-ግብር የተሸከርካሪ የግዥ ፍላጎት የሚሰባሰበው በገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ሆኖ ግዥው እንዲፈጸምለት ሚኒስቴር መ/ቤቱ ለአገልግሎቱ የግዥ ፍላጎት ሲያቀርብና ግዥ የሚፈጸምበትን ገንዘብ ለአገልግሎቱ ሲያስተላልፍ የተሸከርካሪ ግዥ የሚፈጸም መሆኑን፣

25. የክትትል ኦዲት በተከናወነበት ወቅት የሚከተሉት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡-

26. የተሸከርካሪ ግዥ በማዕከል የሚፈፀም ሲሆን ለተሸከርካሪ ግዥ የሚውል በጀት በእያንዳንዱ ባለበጀት መ/ቤት በጀት እንደማይያዝ እና የተሸከርካሪ በጀት የሚያዘው በገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚ/ር በማዕከል መሆኑ፣ የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚ/ር የእያንዳንዱን ባለበጀት መ/ቤት ፍላጎት አሰባስቦ ግዥ እንዲፈፀም ትእዛዝ ሲያስተላልፍ አገልግሎቱ ግዥ የሚፈጽም እንደሆነ ፣

27. በዚህም መሠረት ግዥ ከተፈጸመ በኋላ የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር በሚሰጣቸው ምደባ መሰረት ስርጭት እንደሚያደርጉና አሁንም በዚሁ አግባብ እየተሰራ መሆኑ የአገልግሎቱ የሚመለከታቸው የሥራ ሃላፊዎች በቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ ገልፀዋል፡፡

28. ይሁን እንጂ በአገልግሎቱ የውስጥ መመሪያ ቁጥር 02/2004 ዓ.ም አገልግሎቱ ፍላጎት አሰባስቦ ከሚገዛቸው የማዕቀፍ ዝርዝር እቃዎች ውስጥ የተሸከርካሪ ግዥ የተካተተ ቢሆንም በመመሪያው መሰረት ተግባራዊ አለመደረጉ፣

29. አገልግሎቱ የተሽከርካሪ መለዋወጫዎች፣ የምግብ ጥሬ ዕቃዎች፣ የደንብ ልብሶች፣ የኤሌክትሪክ ዕቃዎችና መሳሪያዎች፣ መፅሐፍትና መፅሔቶች እንዲሁም የህንፃ መሳሪያዎችና የግንባታ ዕቃዎች የመንግስት ግዥና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ

አገልግሎቱ ከዘረዘራቸውና በአገልግሎቱ በኩል ግዥ ያቸው ከሚፈፀም የጋራ መጠቀሚያ ዕቃዎች ውስጥ ያሉ ቢሆንም በአሁኑ ጊዜ ከተዘረዘሩት የጋራ መጠቀሚያ ዕቃዎች ውስጥ የደንብ ልብስ ብቻ በአገልግሎቱ እየገዛ መሆኑን የአገልግሎቱ የሚመለከታቸው የስራ ሀላፊዎች በቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ ገልፀዋል፡፡

30. አገልግሎቱ ለሁሉም የመንግስት ዩኒቨርሲቲዎች በጨረታ ከወጡት ዕቃዎች መካከል 4 የፕሪንተር ቶነሮች እና 5 የፎቶ ኮፒ ማሽን ቶነሮች አቅራቢ ያልተገኘላቸው በመሆኑ ግዥውን በራሳቸው እንዲፈጸም የስራ አመራር ቦርዱ የወሰነ መሆኑ፣

31. አገልግሎቱ በ2008 ዓ.ም ለሁሉም የመንግስት ዩኒቨርሲቲዎች አቅራቢ ካልተገኘላቸው እቃዎች ውስጥ binding ring 22mm፣ 26mm፣ 28mm፣ white board marker፣ canvas plaster 25 metere፣ box file with string paper hard board፣ binding chip 15mm፣ 8mm፣ 5mm፣ እንዲሁም black load pencil፣ እንደሚገኙ እና ግዥው ተሰርዞ ድጋሚ ጨረታ እንዲወጣ የአገልግሎቱ የስራ አመራር ቦርድ በቃለ ጉባኤ የተወሰነ ቢሆንም የክትትል ኦዲቱ እስከተጠናቀቀበት ጊዜ ድረስ ከላይ ለተዘረዘሩት እቃዎች ድጋሚ ጨረታ ስለመውጣቱ ማስረጃው ለኦዲት ቡድኑ አልቀረበም፡፡

32. አገልግሎቱ በ2008 ዓ.ም Note book large size & medium size ለባህርዳር ቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት፤ ለጋምቤላ ዩኒቨርሲቲ፤ ጎንደር ዩኒቨርሲቲና ለመድወላቡ ዩኒቨርሲቲ እንዲሁም CD-R CD-RW ለአዲግራት፤ አርባ ንጭ፤ ደብረ ታቦር እና ዋቻሞ ዩኒ ዩኒቨርሲቲ፤ ለወንዶ ገነት ደንና ተፈጥሮ ሀብት ኮሌጅ፤ ለሀዋሳ ሕክምና ጤና ሳይንስ ኮሌጅ አቅራቢ ባለመገኘቱ ድጋሚ ጨረታ መውጣት ሲገባው ዩኒቨርሲቲዎቹ ግዥውን በማዕከል እንዲፈፅሙ መደረጉን ከቦርድ ቃለ-ጉባኤ ለማወቅ ተችሏል፡፡

33. የቅድመ ክፍያ አፈጻፀምን በተመለከተ የፌዴራል ባለበጀት መ/ቤቶቹ የቴክኒክ ቡድን የእቃውን ትክክለኛነት አረጋግጦ ሞዴል 20 ከተቆረጠ ከአምስት ቀናት በኋላ ክፍያ እንደሚፈጽሙ በናሙና የታዩት ንግድ ሚኔስቴር፣ ትምህርት ሚኒስቴር፣ ማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ኤጀንሲ፣ የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን፣ የኢትዮጵያ የደረጃዎች ኤጀንሲ፣ የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር

ሚኒስቴር እና አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የሚመለከታቸው የስራ ሀላፊዎች በቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ ለማወቅ ተችሏል፡፡

34. ስለጉዳዩ የሚመለከታቸው የአገልግሎቱ የበላይ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ፡-

- አገልግሎቱ የተሸከርካሪ የግዥ ፍላጎት ከፌዴራል መንግስት መስሪያ ቤቶች እንደማያሰባስብ ምክንያቱም ለባለበጀት መ/ቤቶች ለተሽከርካሪ ግዥ ተብሎ የሚፈቀድ የተሸከርካሪ በጀት ስለማይዙ ፍላጎት አያሰባስብም፤ ነገር ግን ከገንዘብ ሚኒስቴር ፍላጎትና በጀትን አጣጥሞ የሚገዙትን ተሽከርካሪዎች ቁጥር ወስኖ በአገልግሎቱ በኩል እንዲገዙ ሲያዝ ግዥ የሚፈጽም በመሆኑ የተነሳ አገልግሎቱ የተሸከርካሪ ግዥ ፍላጎት አሰባስቦ በወጣው ደንብና መመሪያ መሰረት የማዕቀፍ ስምምነት ተፈራርሞ በራሱ ዕቅድ መሰረት ግዥ እንደማይፈጽም ገልጸዋል፡፡
- አገልግሎቱ ካለበት የሰው ሀይል እጥረት የተነሳ የመንግስት ግዥና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ ከዘረዘራቸውና በአገልግሎቱ በኩል ግዥ ያቸው ከሚፈፀም የጋራ መጠቀሚያ ዕቃዎች ዝርዝር ውስጥ ያሉ ቢሆንም በአሁኑ ጊዜ ከተዘረዘሩት የጋራ መጠቀሚያ ዕቃዎች ውስጥ የተሸከርካሪ መለዋወጫዎች፣ የምግብ ጥሬ ዕቃዎች፣ የኤሌክትሪክ ዕቃዎችና መሳሪያዎች፣ መፅሐፍትና መፅሔቶች እንዲሁም የህንፃ መሳሪያዎችና የግንባታ ዕቃዎች ፍላጎት አሰባስቦ ግዥ የማይፈጽም መሆኑና የኤሌክትሪክ እቃዎች፣ መጽሀፍትና መጽሄቶች እንዲሁም የህንጻ መሳሪያዎችና የግንባታ ዕቃዎችን በመደበኛ/በተናጠል/ ግዥ እየፈጸሙ መሆኑን ገልጸዋል፡፡
- አገልግሎቱ በድጋሚ ጨረታ ማውጣቱ ጊዜ ስለሚፈጅና የመጀመሪያው ጨረታ ጊዜ ስለዘገየ በ2008 ዓ.ም ለሁሉም የመንግስት ዩኒቨርሲቲዎች አቅራቢ ካልተገኘላቸው እቃዎች ውስጥ binding ring 22mm፣ 26mm፣ 28mm፣ white board marker፣ canvas plaster 25 metere፣ box file with string paper hard board፣ binding chip 15mm፣ 8mm፣ 5mm፣ እንዲሁም black load pencil፣ እንደሚገኙ እና ግዥው ተሰርዞ ድጋሚ ጨረታ እንዳልወጣላቸው ገልጸዋል፡፡
- አገልግሎቱ በድጋሚ ጨረታ ማውጣቱ ጊዜ ስለሚፈጅና የሰው ሀይል ባለመሟላቱ የተነሳ በ2008 ዓ.ም Note book large size & medium size

ለባህርዳር ቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት፤ ለጎምቤላ ዩኒቨርሲቲ፤ ጎንደር ዩኒቨርሲቲና ለመድወላቡ ዩኒቨርሲቲ እንዲሁም CD-R CD-RW ለአዲግራት፤ አርባ ንጭ፤ ደብረ ታቦር እና ዋቻሞ ዩኒ ዩኒቨርሲቲ፤ ለወንዶ ገነት ደንና ተፈጥሮ ሀብት ኮሌጅ፤ ለሀዋሳ ሕክምና ጤና ሳይንስ ኮሌጅ አቅራቢ ባለመገኘቱ ድጋሚ ጨረታ መውጣት ሲገባው ዩኒቨርሲቲዎቹ ግዥውን በማዕከል እንዲፈፅሙ መደረጉን ገልጸዋል፡፡

35. የአገልግሎቱ የበላይ ኃላፊዎች ይህን ይበሉ እንጂ የተሽከርካሪ አቅም ታይቶ በማዕከል ስለመገዛቱና የመድህን አገልግሎትም ለ3 ዓመታት የሚያገለግል አጠቃላይ ውል ፍላጎት ስለመሰባሰቡ የግዥና የውል አስተዳደር የውስጥ አሰራር መመሪያው ከመውጣቱ በፊት የሚታወቅ ከነበረ መመሪያው ላይ መካተት ያልነበረበት በመሆኑና መመሪያው ከወጣ በኋላም የታወቀ ከሆነ መመሪያውን ማሻሻል ወይም እስኪሻሻል የተፈቀደ የፅሁፍ መረጃ እንዲኖር መደረግ ይገባ የነበረ በመሆኑ፤ በተጨማሪም binding ring 22mm፣ 26mm፣ 28mm፣ white board marker፣ canvas plaster 25 metere፣ box file with string paper hard board፣ binding chip 15mm፣ 8mm፣ 5mm፣ እንዲሁም black load pencil፣Note book large size & medium size፣ CD-R CD-RW ድጋሚ ጨረታ ማውጣቱ ተጨማሪ ጊዜ ስለሚወስድና ስራ እንዳይበደል በማሰብ ተግባራዊ ያልተደረገ መሆኑን በተመለከተ ደግሞ መመሪያው የተጣሰው ድጋሚ ጨረታ ማውጣት እንደሚቻል ቀደም ብሎ ባለመታሰቡ የዕቅድ ችግር መኖሩን የሚያመለክት በመሆኑ የግዥና የውል አስተዳደር መመሪያው በራሱ በአገልግሎቱና በአቅራቢዎች በተገቢው መንገድ ተግባራዊ አለመደረጉን የሚያመለክት በመሆኑ የተሰጠውን መልስ አልተቀበልነውም፡፡

አገልግሎቱ የባለበጀት መ/ቤቶችን የግዥ ፍላጎት ማሰባሰብ፣ መለየትና ማደራጀትን <u>በተመለከተ፤</u>

36. በክዋኔ ኦዲቱ ወቅት የተገኘው፤

37. አገልግሎቱ በ2003 ዓ.ም. ለ2004 በጀት ዓመት ግዥ የፍላጎት ማሳወቂያ ደብዳቤ ከመጋቢት ወር በፊት ቀድሞ መላክ ሲገባው የፍላጎት ማሳወቂያ ደብዳቤውን የላከው ማሰባሰብ ካለበት 5 ወር ዘግይቶ በ22/11/03 የላከ መሆኑ፣ በ2004 ዓ.ም. ለ2005 በጀት ዓመት ማሰባሰብ ከነበረበት ጊዜ ከ2-8 ወራት ዘግይቶ እስከ ጥቅምት 20/2005ዓ.ም የላከ መሆኑ፣

38.በ2005 ዓ.ም. ለ2006 በጀት ዓመት ግዥ ፍላጎት ደግሞ የካቲት 27/2005 ዓ.ም. የመ/ቤቶችን የግዥ ፍላጎት እንዲያሳውቁት የጠየቀ ቢሆንም አገልግሎቱ ከመጋቢት1 ጀምሮ ፍላጎት የሚያሰባስብበት ጊዜ ስለሆነ የመንግስት መ/ቤቶችም በ3 ቀናት ውስጥ ከዕቅዳቸው በመነሳት ፍላጎታቸውን ሞልተው ለመላክ በቂ ጊዜ ስላልተሰጣቸውና በተባለው ጊዜ ፍላጎት መላክ እንዳልቻሉ እና የግዥ ሂደቱ እንዲጓተት ያደረገ መሆኑ፣

39.በጋራ የሚፈለጉ ዕቃዎች ላይ የገበያ ጥናት ባለመኖሩ አገልግሎቱ ከባለበጀት መ/ቤቶች የተሰበሰበውን ፍላጎት በገበያ ጥናት መሰረት ዕቃው በገበያ ላይ ስለመኖሩ በማረጋገጥ እንደማያደራጅ ተገኝቶ ነበር፡፡

40.አገልግሎቱ ለቀጣይ በጀት ዓመት የሚገዙ ግዥዎችን ከመ/ቤቶች የግዥ ዕቅድ ጋር የተጣጣመ እንዲሆን የመ/ቤቶችን የግዥ ፍላጎት በየዓመቱ ከመጋቢት 1 ቀን እስከ ሚያዚያ 30 ቀን ድረስ ባለው ጊዜ ሊለይና ሊያሰባስብ እንዲሁም ከባለበጀት መ/ቤቶች በቀረበው የግዥ ፍላጎት መሰረት በመንግስት ግዥና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ የተወሰኑትን ግዥዎች በአስር የስራ ቀናት ውስጥ በዓይነት፣ በመጠን፣ በጥራት ደረጃ እና በሚገኝበት ቦታ በተለያየ ምድብ /በሎት/ መድቦና አደራጅቶ ሊይዝና ለግዥው አፈፃፀም አመቺ ሁኔታ ለመፍጠር እንዲያስችል ተመሳሳይና ተቀራራቢ ፍላጎቶችን አንድ ላይ በማሰባሰብ ከገበያ ጥናት የተገኘውን መረጃ መሰረት በማድረግ ሊያደራጅ እንደሚገባ የማሻሻያ ሀሳብ ተሰጥቶ ነበር፡፡

41.አገልግሎቱ ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት በደብዳቤ ቁጥር ግንማ 14/1/12/8265 ጥር 18 ቀን 2007 ዓ.ም. አዘጋጅቶ በላከው የድርጊት መርሃ-ግብር ከ2006 በጀት ዓመት ጀምሮ በመንግስት ግዥና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ ዌብሳይት የጋራ መጠቀሚያ እቃዎችና አገልግሎቶች ዝርዝር መሰረት መስሪያ ቤቶች የግዥ ፍላጎታቸውን እንዲያቀርቡ እንደሚደረግ፣

42.አገልግሎቱ የሚያከናውነውን ስራ ለባለድርሻ አካላትና ለተገልጋዮች የማስተዋወቅ ስራ የጋራ የመወያያ መድረክ በመፍጠር እየሰራ የሚገኝና ለወደፊቱ የበለጠ ለማጠናከር ከባለድርሻ አካላት ጋር ቅንጅታዊ ስራ ታቅዶ የሚሰራ መሆኑ እና የተከናወኑ የእቃና አገልግሎት ግዥዎች በዕቅዱ መሰረት ተግባራዊ ስለመደረጉ የዕቅድ ክንውን ሪፖርት እንደሚያዘጋጅ ፣

43.አገልግሎቱ ከ2008 በጀት ዓመት ጀምሮ የሚያዘጋጀው የግዥ ዕቅድ የሚገዛውን እቃና አገልግሎት ዓይነት፣ ግዥው የሚፈጸምበትን የገንዘብ ምንጭ የግዥው

ምድብ፣ ለግዥው የተያዘው የበጀት ግምት፣ የተመረጠውን የግዥ ዘዴ፣ ግዥውን ለመፈጸም የሚወስደው ጊዜ፣ ጨረታ የሚወጣበት/ የሚካሄድበት እና ግዥው ተጠናቆ ርክክብ የሚፈፀምበት ጊዜ የግዥ እቅድ ውስጥ በማካተት እንደሚዘጋጅ እና እቅዱን ለመንግስት ግዥና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ እንደሚያቀርብ፣

44. አገልግሎቱ ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት በደብዳቤ ቁጥር ግንማ 14/1/12/8265 ጥር 18 ቀን 2007 ዓ.ም. አዘጋጅቶ በላከው የድርጊት መርሃ-ግብር አገልግሎቱ ከ2007 በጀት ዓመት ጀምሮ የመ/ቤቶችን የግዥ ፍላጎት እንዲያሳውቁ በቂ ጊዜ ተሰጥተው በወቅቱ ፍላጎታቸውን እንዲያቀርቡ እያደረገ መሆኑ፤ ከ2006 በጀት ዓመት ጀምሮ ግዥዎች በዓይነት፣ በመጠን፣ በጥራት ደረጃ እና በተለያዩ ምድብ /በሎት/ የሚመድብበት አሰራር እና የገበያ ጥናት ስራ እንደሚደረግ ገልጸዋል፡፡

45. የክትትል ኦዲት በተከናወነበት ወቅት የሚከተሉት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡-

46. አገልግሎቱ ለባለበጀት መ/ቤቶች የግዥ ፍላጎታቸውን እንዲያቀርቡ ቢያንስ ከአንድ ወር በላይ ጊዜ እንደሚሰጣቸው እና ፍላጎታቸውን ያላቀረቡ ባለበጀት መ/ቤቶች እና የመንግስት ዩኒቨርሲቲዎች መኖራቸውና የግዥ ፍላጎታቸውን ለአገልግሎቱ ሳያሳውቁ ግዥ እንደሚፈጽሙ የአገልግሎቱ የሚመለከታቸው የስራ ሃላፊዎች ከቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ ታውቋል፡፡

47. አገልግሎቱ ከባለበጀት መ/ቤቶች የሚያሰባስበውን የግዥ ፍላጎት መሠረት በማድረግ ለእያንዳንዱ ግዥ ዝርዝር የፍላጎት ማረጋገጫ ሰነድ አዘጋጅቶ በዚህ የፍላጎት ማረጋገጫ ሰነድ ላይ በዓይነትና በመጠን እንዲሁም በተለያየ ምድብ /በሎት/ የራሱ የሆነ ክፍል አዘጋጅቶ እንደሚያደራጅ የኦዲት ቡድኑ ባደረገው ምልከታ ለማወቅ ተችሏል፡፡

48. አገልግሎቱ የግዥ ፍላጎት መጠየቂያ ደብዳቤ በወቅቱ የሚልክ ቢሆንም አገልግሎቱ የማይገዛቸው በጋራ የሚፈለጉ እቃዎች ዝርዝር ዘግይቶ ስለሚያሳውቅ መ/ቤቶቹ ወደ ፕሮፎርማ ግዥ እንደሚገቡ፤ እንዲሁም የግዥ እቅዳቸውን በየዓመቱ ለአገልግሎቱ እንደሚልኩ፣ ነገር ግን የፈለጉትን ዕቃ መጠን በሚፈልጉበት ጊዜ እንደማያገኙ በናሙና የታዩት ንግድ ሚኔስቴር ፣ ትምህርት ሚኒስቴር፣ ማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ኤጀንሲ፣ የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስጣን፣ የኢትዮጵያ የደረጃዎች ኤጀንሲ፣ የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር እና አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የስራ ሀላፊዎች በክትትል ኦዲቱ ወቅት በቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ ገልፀዋል፡፡

49. ስለጉዳዩ የሚመለከታቸው የአገልግሎቱ የበላይ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ:-

- የግዥ ፍላጎታቸውን ያላቀረቡ ባለበጀት መ/ቤቶች እና የመንግስት ዩኒቨርሲቲዎች ግዥ እንዳይፈጽሙ የሚል ስርዓት ስለሌለ/ስላልተዘረጋ/ ግዥ አትፈጽሙ የሚል ውሳኔ ማሳለፍ አለመቻሉ፣ በዚህ የተነሳ የግዥ ፍላጎታቸውን ያላቀረቡ ባለበጀት መ/ቤቶች እና የመንግስት ዩኒቨርሲቲዎች መኖራቸውና የግዥ ፍላጎታቸውን ለአገልግሎቱ ሳያሳውቁ ግዥ እንደሚፈጽሙ ገልጸዋል፡፡
- አገልግሎቱ የግዥ ፍላጎታቸውን ያላቀረቡ ባለበጀት መ/ቤቶች እና የመንግስት ዩኒቨርሲቲዎች በመኖራቸው ምክንያት የመንግስት መ/ቤቶች የፈለጉትን ዕቃ መጠን በሚፈልጉበት ጊዜ እንደማያገኙና ወደ ፕሮፎርማ ግዥ እንደሚገቡ ገልጸዋል፡፡

50. የአገልግሎቱ የበላይ ኃላፊዎች ይህን ይበሉ እንጂ የተሰጠውን መልስ አልተቀበልነውም ምክንያቱም የፌዴራል ባለበጀት መ/ቤቶች እና የመንግስት ዩኒቨርሲቲዎች የግዥ ፍላጎት እንዲያሳውቁ የሚያስገድድ እና ፍላጎታቸውን ለማያሳውቁ አካላት የተጠያቂነት አሰራር በመመሪያ ውስጥ ሊካተት እንደሚገባ ይታመናል፡፡

አገልግሎቱ ባዘጋጀው ስትራቴጅክ ዕቅድ መሠረት ዓመታዊ የግዥ ዕቅድ ማዘጋጀቱን፣ ዕቅዱን ተግባራዊ ማድረጉን እንዲሁም የዕቅድ ክንውን ሪፖርት ማቅረቡን <u>በተመለከተ፤</u>

51. በክዋኔ ኦዲቱ ወቅት የተገኘው፡-

52. የአገልግሎቱ ከ2003-2007 ዓ.ም የውጤት ተኮር ስርዓት የ5 ዓመት ስትራቴጂክ ዕቅድ ሲታይ የትኛው ተግባር በየትኛው ዓመት እንደሚሰራ ተለይቶና በስትራቴጂው የታቀደው ተግባር ከዓመታዊ ዕቅድ ጋር በየዓመቱ በተጣጣመ መልኩ ያልተቀመጠ መሆኑ ተገኝቶ ነበር፡፡

53. በስትራቴጅክ ዕቅድ መሰረት በየዓመቱ ተመንዝረው የሚታቀዱ ተግባራት የመ/ቤቱን የስራ አፈፀፃም ለመለካትና የማሻሻያ ሃሳብ ለመውሰድ እንዲያስችል አገልግሎቱ በግልፅና በመቶኛ፣ የትኛው ተግባር በየትኛው ዓመት እንደሚሰራ

ሊያስቀምጥ፣ ዕቅድ ክንውን ሪፖርት ሊያቀርብ እንደሚገባ የማሻሻያ ሀሳብ ተሰጥቶ ነበር፡፡

54. አገልግሎቱ ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት በደብዳቤ ቁጥር ግንማ 14/1/12/8265 ጥር 18 ቀን 2007 ዓ.ም. አዘጋጅቶ በላከው የድርጊት መርሃ-ግብር ላይ ስለጉዳዩ የገለፀው ነገር የለም፡፡

55. የክትትል ኦዲት በተከናወነበት ወቅት የሚከተሉት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡-

56. ከ2008-2012 ዓ.ም ያለው አመታዊ እቅድ ስትራቴጂካዊ እቅዱ ጋር በተጣጣመ መልኩ ያልተዘጋጀ መሆኑን ከተከለሱ ማስረጃዎች ለማወቅ የተቻለ ሲሆን፣ የአገልግሎቱ የሚመለከታቸው የሥራ ሃላፊዎች በቀረበላቸው ቃለ-መጠይቅ የቀጣይ ስትራቴጅክ እቅድ ከአመታዊ እቅዱ ጋር በማጣጣም እንደሚዘጋጅ የገለፁ መሆኑ፣

57. አገልግሎቱ የግዥ ስርዓቱን ለማሻሻል ከሚመለከታቸው የመንግስት መ/ቤቶችና ከግሉ ዘርፍ ጋር ዘመናዊ የመረጃ ልውውጥ፣ ክትትል፣ በቴክኖሎጂ የመጠቀም ስርዓት ተግባራዊ የማድረግና የተሻለና ጥራቱን የጠበቀ የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ አቅርቦት ለባለድርሻ አካላት በሚመች መልኩ የማዘጋጀት ስራዎችን በተመለከተ እንደ ሀገር የግዥ ሥርዓት ማሻሻያ e-procurement ተግባራዊ የማድረግ ኃላፊነት የመንግስት ግዥና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ እየሄደበት ያለ ጉዳይ እንደሆነ፣ ነገር ግን በአገልግሎቱ ከመንግስት መ/ቤቶችና ከግል ዘርፉ ጋር ዘመናዊ የመረጃ ልውውጥ እንዲኖር ጅምር ሥራዎች መኖራቸውና በተሟላ መልኩ እየተካሄደበት እንዳልሆነ የአገልግሎቱ የሚመለከታቸው የስራ ሀላፊዎች በቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ ገልፀዋል፡፡

58. አገልግሎቱ የማዕቀፍ እና ስትራቴጅክ ግዥዎች በ2009 በጀት ዓመት በ7.5 ቢሊዮን ብር ግዥ የተፈጸመ ሲሆን አፈጻጸሙ ከ2008 በጀት ዓመት ጋር ሲነጻጸር 40% ዝቅ ያለ እንደሆነ ከአገልግሎቱ የስራ አመራር ቦርድ ቃለ-ጉባኤ ለማወቅ ተችሏል፡፡

59. አገልግሎቱ ከባለበጀት መ/ቤቶችና አቅራቢዎች ጋር ያለው የመረጃ ልውውጥ በደብዳቤ ብቻ እንደሆነና ዘመናዊ የመረጃ ልውውጥ እንደሌለው፣ ከባለድርሻ አካላት ጋር ግዥን በተመለከተ ካደረገው ውይይት በስተቀር አገልግሎቱ ስለሚሰራው ስራ እና ከኤጀንሱ ጋር ስላለው ልዩነት የግንዛቤ ማስጨበጫ

እንዳልተሰጣቸውና የጋራ የመግባቢያ ስምምነት ሰነድ እንዳልተፈራረሙ በክትትል ኦዲቱ ወቅት በናሙና የታዩ ንግድ ሚኔስቴር ፣ ትምህርት ሚኒስቴር፣ ማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ኤጀንሲ፣ የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስጣን፣ የኢትዮጵያ የደረጃዎች ኤጀንሲ፣ የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር እና አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣

60. እንዲሁም ከአቅራቢዎች መካከል ናሽናል ማርኬተርስ፣ ራዲካል ኃ.የተ.የግ.ኩ ድርጅቶች የሚመለከታቸው የስራ ሀላፊዎች በቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ ገልፀዋል፡፡

61. ስለጉዳዩ የሚመለከታቸው የአገልግሎቱ የበላይ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ፡-

- በ2008 በጀት ዓመት ከተገዛው ስትራቴጂክ ግዥ ውስጥ የስንዴ መጠን ብዛት ስለነበረው የ2008 በጀት ዓመት ከ2009 በጀት አመት ሲነጻጸር 40% ከፍ ማለቱን ገልጸዋል፡፡
- አገልግሎቱ ዘመናዊ የመረጃ ልውውጥ ስርዓት ለመዘርጋት የተመደቡ ባለሙያዎች በመልቀቃቸው ምክንያት ከባለበጀት መ/ቤቶች፣ የመንግስት ዩኒቨርሲቲዎችና አቅራቢዎች ጋር ያለው የመረጃ ልውውጥ በደብዳቤ ብቻ እንደሆነና ዘመናዊ የመረጃ ልውውጥ ስርዓት እንዳልተዘረጋ ገልጸዋል፡፡

62. ይሁን እንጂ፡-

- አገልግሎቱ የግዥ ዕቅዱን በግዥ አፈፃፀም መመሪያ አንቀጽ 12 (የግዥ ዕቅድ ይዘትን በተመለከተ) እና በዓመታዊ የግዥ ዕቅድ ማቅረቢያ ሠንጠረዥ አባሪ 1 መሰረት የግዥ ዕቅዱን ያላዘጋጀ መሆኑ፡፡
- አገልግሎቱ በአዋጅ የተሰጠውን ስልጣንና ተግባር ለመፈፀምና ከአገልግሎቱ ሊገኝ የሚችለውን ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ በቅልጥፍናና ውጤታማ በሆነ አሰራር ለማግኘት እንዲቻል በተሟላ የሰው ኃይልና ድርጅታዊ አቅም በመገንባት ከባለበጀት መ/ቤቶች፣ የመንግስት ዩኒቨርሲቲዎችና አቅራቢዎች ጋር ዘመናዊ የመረጃ ልውውጥ ስርዓት መዘርጋት እንደነበረበት ይታመናል፡፡

የመንግስት መ/ቤቶች የሚጠቀሙባቸውን ተመሳሳይ ዕቃዎችና አገልግሎቶች ዝርዝር ተጠንቶ የግዥ አገልግሎት ስለመከናወኑ፤

63. በክዋኔ ኦዲቱ ወቅት የተገኘው፤

64. የመንግስት ግዥና ንብረት ማስወገድ አገልግሎት ዝርዝራቸው በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ለሚወሰን የመንግሥት ባለበጀት መ/ቤቶች በጋራ ለሚፈለጉ እቃዎች የግዥ ውል ከመፈራረም ውጭ የዕቃ ግዥ የማያከናውን መሆኑ፤ እንዲሁም ለአገልግሎት ግዥም የግዥ ውል እንደማይፈራረም እና ግዥም እንደማያከናውን ተገኝቶ ነበር፡፡

65. የመንግሥት ግዥና ንብረት ማስወገድ አገልግሎት ሀገሪቷ ከከፍተኛ ግዥ የሚገኘውን ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ለማግኘት እንድትችል የመንግስት መ/ቤቶች የሚጠቀሙባቸውን ተመሳሳይ ዕቃዎችም ሆነ አገልግሎቶች ግዥ በማቋቋሚያ ደንቡ በተሰጠው ስልጣን መሰረት የመ/ቤቱን አቅም በማሳደግና የራሱ ዕቃዎችን ገዝቶ የሚያስቀምጥበት የዕቃ መጋዘን በመሥራት/እንዲኖር በማድረግ መ/ቤቶችም ለጋራ መጠቀሚያ ዕቃዎች የሚያውሉት በጀት በአንድ ማዕከላዊ በሆነ አካውንት እንዲከቱ በማድረግና ለመንግሥት መ/ቤቶች ዕቃዎችን እስከ ማስረከብ ያለውን የግዥ ሂደት ሥራ ሊሰራ እንደሚገባ የማሻሻያ ሀሳብ ተሰጥቶ ነበር፡፡

66. አገልግሎቱ ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት በደብዳቤ ቁጥር ግንማ 14/1/12/8265 ጥር 18 ቀን 2007 ዓ.ም አዘጋጅቶ በላከው የድርጊት መርሃ-ግብር አገልግሎቱ በፌዴራል መንግስት የግዥ አፈጻጸም መመሪያ አንቀፅ 27 ንዑስ አንቀጽ 10 ላይ በተገለጸው መሰረት የማዕቀፍ ስምምነት በመፈጸም ለፌዴራል የመንግስት መ/ቤቶች ቅጅውን ያስተላልፋል፣ በዚሁ መሰረት መ/ቤቶች ግዥ እንዲፈጽሙ ማድረግ እንጂ የማዕቀፍ ግዥ የመፈጸም ኃላፊነት እንዳልተሰጠው ገልጿል፡፡

67. የክትትል ኦዲት በተከናወነበት ወቅት የሚከተሉት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡-

68. አገልግሎቱ ዝርዝራቸው በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ለሚወሰን የመንግሥት ባለበጀት መ/ቤቶች በጋራ ለሚፈለጉ እቃዎች የግዥ ውል ከመፈፀም ውጭ የእቃ ግዥ የማይፈፅም መሆኑ፣ ከኢንሹራንስ መድህን አገልግሎት ውጭ ሌሎች የአገልግሎት ግዥዎችን እንደማይፈጽም የአገልግሎቱ የሚመለከታቸው የስራ ሃላፊዎች ከቀረበላቸው ቃለ መጠየቅ ለመረዳት ተችሏል፡፡

69. አገልግሎቱ የመንግስት ግዥና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ በጋራ መጠቀሚያ ዕቃዎች ዝርዝር ካካተታቸው ዕቃዎች ውስጥ አገልግለቱ አቅሙ በፈቀደው መጠን

ሊገዛቸው የሚችላቸውን ዕቃዎች እየለየ ግዥ እየፈፀመ መሆኑ፣ አገልግሎቱ ከተቋቋመ ጀምሮ በየዓመቱ የሚገዛቸው የጋራ መጠቀሚያ ዕቃዎች እየጨመሩ መሆኑ የአገልግሎቱ የሚመለከታቸው የሥራ ሀላፊዎች በቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ ገልፀዋል፡፡

70. ስለጉዳዩ የሚመለከታቸው የአገልግሎቱ የበላይ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ አገልግሎቱ በወቅቱ የወጣው መመሪያ ከኮሪያ መልካም ተሞክሮ ተቀምሮ የመጣ መሆኑና መ/ቤቱ በተቋቋመበት ወቅት በነበረው ጉጉት በውስጥ መመሪያው የተካተተ መሆኑ፣ ነገር ግን ካለው ነባራዊ ሁኔታ አንጻር ተግባራዊ ለማድረግ የማይቻል በመሆኑ የተነሳ የመንግሥት ግዥና ንብረት ማስወገድ አገልግሎት ሀገሪቷ ከከፍተኛ ግዥ የሚገኘውን ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ለማግኘት እንድትችል የመንግስት መ/ቤቶች የሚጠቀሙባቸውን ተመሳሳይ ዕቃዎችም ሆነ አገልግሎቶች ግዥ በማቋቋሚያ ደንቡ በተሰጠው ስልጣን መሰረት የመ/ቤቱን አቅም በማሳደግና የራሱ ዕቃዎችን ገዝቶ የሚያስቀምጥበት የዕቃ መጋዘን በመሥራት መ/ቤቶች ለጋራ መጠቀሚያ ዕቃዎች የሚያውሉት በጀት በአንድ ማዕከላዊ በሆነ አካውንት እንዲከቱ በማድረግና ለመንግሥት መ/ቤቶች ዕቃዎችን እስከ ማስረከብ ያለውን የግዥ ሂደት ሥራ እንደማይሰራ ገልጸዋል፡፡

71. ይሁን እንጂ ይህ ጉዳይ የታወቀው መመሪያው ከተዘጋጀ በኋላ ቢሆንም የክትትል ኦዲቱ እስከተጠናቀቀበት ጊዜ ድረስ መመሪያው ያልተሻሻለ መሆኑ፡፡

አገልግሎቱ በሚፈለገው ጊዜና መጠን በጋራ የሚፈለጉ ዕቃዎችና አገልግሎቶች ግዥ በማከናወን ለተጠቃሚዎች ማድረስን በተመለከተ፤

72. በክዋኔ ኦዲቱ ወቅት የተገኘው፤

73. በአገልግሎቱ ከቀረቡ የመ/ቤቶች የግል ማህደር በናሙና እንደታየው በ2004 እና በ2005 በጀት ዓመት ግዥዎች ላይ 19 የመንግስት መ/ቤቶች አገልግሎቱ በጀመረው የግዥ ሂደት የግዥ ትዕዛዝ ያስተላለፉበት ዕቃ በሚፈለገው መጠንና ጊዜ ተከታትሎ እንዲደርሳቸው አለማድረጉ ተገኝቶ ነበር፡፡

74. አገልግሎቱ የመንግሥት መ/ቤቶች ዕቃዎችን በሚፈልጉት መጠንና ጊዜ እየደረሳቸው መሆኑን ሊከታተልና በወቅቱ ካላገኙ አስፈላጊውን ድጋፍ በማድረግ ለተጠቃሚው አካላት እንዲደርሱ ሊያደርግ፣

75. አገልግሎቱ ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት በደብዳቤ ቁጥር ግንግ 14/1/12/8265 ጥር 18 ቀን 2007 ዓ.ም. አዘጋጅቶ በላከው የድርጊት መርሃ-ግብር የፌዴራል

መንግስት መ/ቤቶች በጋራ የሚፈለጉ እቃዎችና አገልግሎቶች የግዥ ሂደት በማጠናቀቅ እቃዎችና አገልግሎቶች በሚፈለገው መጠንና ጊዜ ለተጠቃሚው አካላት እንዲደርሳቸው ክትትል እየተደረገ እንደሚገኝና በቀጣይም ክትትሉን በማጠናከር እንደሚሰሩ ገልጿል፡፡

76. የክትትል ኦዲት በተከናወነበት ወቅት የሚከተሉት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡-

77. አገልግሎቱ ለ16 መ/ቤቶች ሌላ አሸናፊ አቅራቢ ድርጅት ጋር ተመድበው መግዛት እንዲችሉ አገልግሎቱን ጠይቀው ክምችት እንደሌላቸውና ዕቃዎቹ ወደ ሀገር ውስጥ እንደሚያስገቡ መ/ቤቶቹ ተከታትለው ግዥ እንዲፈፅሙ የበጀት ዓመቱ መጨረሻ አካባቢ አገልግሎቱ ለመ/ቤቶቹ ያሳወቀ ቢሆንም መ/ቤቶቹ ለረጅም ጊዜ በመመላለስ እቃዎቹን ማግኘት ባለመቻላቸው የግዥ ትዕዛዙን የሰረዙ መ/ቤቶች መኖራቸውን ከክትትል ኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎች ታውቋል፡፡

78. በአገልግሎቱና በመ/ቤቶቹ በተደረገው የፅሁፍ ልውውጦች እንደተመለከተው አቅራቢዎች ጋር ሂደው የግዥ ትዕዛዝ ያስተላለፉበት ዕቃ በመጋዘናቸው ውስጥ የሌለ መሆኑ እንደገለፁላቸው እና አገልግሎቱም ለአንድ ጊዜ ብቻ ከሌሎች አቅራቢዎች በራሳቸው ግዥ እንዲፈጽሙ እንደፈቀደ፣

79. በ2009 በጀት ዓመት ለትምህርት ሚኒስቴርና ለጎንደር ዩኒቨርሲቲ የተጠየቁ ግዥዎች መጓተታቸው፣ የ11ዱ ዩኒቨርሲቲዎች ግዥ በተመለከተ የቴክኒክ ግምገማ መዘግየትና ግዥ በሚፈለገው መጠን አለመከናወኑ፣ እንዲሁም በ2008 ዓ.ም የተጀመሩ ከ48 ግዥዎች ውስጥ 32ቱ እንዳልተጠናቀቁ ከአገልግሎቱ የስራ አመራር ቦርድ ቃለ-ጉባኤ ለማወቅ ተችሏል፡፡

80. አገልግሎቱ በናሙና የታዩት የተለያዩ መ/ቤቶች የሚፈልጉትን ዕቃዎችና አገልግሎቶች በሚፈልጉት ጊዜና መጠን በአግባቡ እየደረሳቸው እንዳልሆነ፣ አቅራቢዎች እቃው በመጋዘናቸው እንደሌለ፣ ሊያቀርቡላቸው እንደማይችሉ በናሙና የታዩ የተለያዩ መ/ቤቶች የሚመለከታቸው የሥራ ሀላፊዎች በቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ ገልፀዋል፡፡

81. የአገልግሎቱ የሚመለከታቸው የሥራ ሃላፊዎች ለመንግስት መ/ቤቶች በጋራ የሚፈለጉ ተመሳሳይ ዕቃዎችና አገልግሎቶች በሚፈለገው መጠንና ጊዜ እንዲደርሳቸው እያደረገ መሆኑን ቢገልፁም የ2008-2010 ዓ.ም የግዥ ሂደቱ ተጠናቆ ውል የተገባው ዘግይቶ ህዳር 2008 መሆኑን፣

82. ቀድም ሲል የ2008-2010ዓ.ም ግዥ ሊፈፀም ሲታሰብ ዕቃዎችና አገልግሎቶች በሚፈለገው መጠንና ጊዜ ለተጠቃሚው አካላት መድረሳቸውን የሚከታተል ቡድን መደበኛ በሆነ መልኩ ያልተቋቋመ መሆኑ፣ የተለያዩ መ/ቤቶች የሚፈልጉትን ዕቃዎችና አገልግሎቶች በአግባቡ እየደረሳቸው እንዳልሆነ የተለያየ ቅሬታዎች እያቀረቡ መሆኑን በክትትል ኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎች ለማወቅ ተችሏል፡፡

83. ስለጉዳዩ የሚመለከታቸው የአገልግሎቱ የበላይ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ:-

- አገልግሎቱ የቴክኒክ ግምገማው ረዘም ያለ ጊዜ ስለወሰደና የግዥ ሂደቱ በመዘግየቱ ምክንያት በ2009 በጀት ዓመት ለትምህርት ሚኒስቴርና ለጎንደር ዩኒቨርሲቲ የተጠየቁ ግዥዎች መጓተታቸው፣ የ11ዱ ዩኒቨርሲቲዎች ግዥ በሚፈለገው መጠን አለመከናወኑ፣ እንዲሁም በ2008 ዓ.ም የተጀመሩ ከ48 ግዥዎች ውስጥ 32ቱ ሊጠናቀቁ እንዳልቻሉ ገልጸዋል፡፡
- አገልግሎቱ ለርክክብ ክትትል እንዲመቸው ለሁሉም የፌዴራል መንግስት ባለበጀት መ/ቤቶችና ዩኒቨርሲቲዎች የርክክብ ጊዜ ሰሌዳ ለተመደቡበት አቅራቢዎች እንዲያሳውቁና በግልባጭም ለአገልግሎቱ እንዲልኩ ስኩላር እንዳስተላለፉ፣ ነገር ግን ከ134 የፌዴራል ባለበጀት መ/ቤቶች መካከል 45ቱ ብቻ እንደላኩና ከ45 የመንግስት ዩኒቨርስቲዎች መካከል 14ቱ ብቻ የርክክብ ጊዜ ሰሌዳቸውን እንደላኩ ገልጸዋል፤
- በተጨማሪም በአገልግሎቱ ራሱን ችሎ የተደራጀ ክፍል ባለመኖሩና ጉዳዩንም በጥብቅ ክትትል የሚያደርግ ባለሙያ ባለመኖሩ ምክንያት ባለበጀት መ/ቤቶች ዕቃው በሚፈለገው መጠንና ጊዜ እየደረሳቸው እንዳልሆነና በሚፈለገው ደረጃ ክትትል ማድረግ እንዳልቻሉ ገልጸወዋል፡፡

84.የአገልግሎቱ የስራ ኃላፊዎች ይህን ይበሉ እንጂ አገልግሎቱ ከላይ የተጠቀሱትን ሁኔታዎች ግምት ውስጥ በማስገባት የግዥ ሂደቱን /ፍላጎት ከማሰባሰብ እስከ ውል መፈራረምና የጨረታ አሸናፊ አቅራቢ ድርጅቶ እስከማሳወቅ ያለውን/ በጊዜ ሊያከናውንና በኦዲቱ ወቅት አብዛኛው መ/ቤቶች በሚፈልጉት ጊዜ ያላገኙና በመጠንም ያላገኑ መ/ቤቶች መኖራቸውና ይህንንም ለአገልገሎቱ ማሳወቃቸውን ለአገልግሎቱ በጻፉት ደብዳቤ ለማወቅ ስለተቻለ አገልግሎቱ ይህንን ተከታትሎ

ለመ/ቤቶች በሚፈልጉት ጊዜና መጠን እንዲያገኙ ድጋፍ አለማድረጉ ተገቢ ሆኖ አላገኘነውም፡፡

የመንግሥት ግዥና ንብረት ማስገወድ አገልግሎት የግዥ ሂደት ከመንግስት መ/ቤቶች <u>የበጀት አመት /ፕሮግራም/ ጋር የተጣጣመ መሆኑን በተመለከተ፤</u>

85. በክዋኔ ኦዲቱ ወቅት የተገኘው፤

86. የመንግስት መ/ቤቶች የበጀት ዓመት ከሐምሌ 1 እስከ ሰኔ 30 ቢሆንም በአገልግሎቱ አብዛኛውን ጊዜ መ/ቤቶች ግዥ እንዲፈፅሙ የሚደረገው የበጀት ዓመቱ 1ኛ ሩብ ዓመት ካለፈ በኋላ በመሆኑ አገልግሎቱ የግዥ ሂደቱን ከመንግስት መ/ቤቶች የበጀት ዓመት/ፕሮግራም/ ጋር የተጣጣመ በማድረግ የግዥ መፈፀሚያ ጊዜን አለመወሰኑ ተገኝቶ ነበር፡፡

87. በግዥ አፈፃፀም መመሪያ መሠረት የባለበጀት መ/ቤቶች የስራ ፕሮግራማቸውን ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስፈልገውን ግገር በወቅቱ ለመፈፀም እንዲያስችላቸው የግገር ፍላጎት መሰረት በመርሐ-ግብር የተደገፈ የሚገዛውን ዕቃና አገልግሎት ዓይነት፣ ግዥው የሚፈፀምበትን የገንዘብ ምንጭ፣ የግዥው ምድብ፣ ለግዥው የተያዘው የበጀት ግምት፣ የተመረጠው የግዥ ዘዴ የግዥው ዓይነትና ግዥን ለመፈጸም የሚወስደው ጊዜ /ጨረታ የሚወጣበት ወይም የሚካሄድበት፣

88. ግዥው ተጠናቆ ርክክብ የሚፈፀምበትን ዕቅድ በማዘጋጀት የታወቁትን የግዥ ፍላጎቶች በሙሉ በግዥ ዕቅዱ ውስጥ እና እንደ ግዥ ሁኔታ ለእያንዳንዱ ግዥ ተስማሚ የሆነ የግዥ ዘዴ በመምረጥ ማመላከት እና ለባለበጀት መ/ቤቶችና ለኤጀንሲው ሊያሳውቅ እንደሚገባ የማሻሻያ ሀሳብ ተሰጥቶ ነበር፡፡

89. የመንግስት መ/ቤቶች የተመደበላቸውን የግዥ ገንዘብ በበጀት ዓመቱ ለመጠቀም እንዲያስችላቸውና አላስፈላጊ የግዥ ዘዴ ውስጥ እንዳይገቡ የግዥ ፍላጎት ለመ/ቤቶች በጊዜ በመላክና አመታዊ የግዥ ዕቅድ በማውጣት የሚፈጽመውን ግዥ ከመ/ቤቶች የበጀት አመት /ፕሮግራም/ጋር በማጣጣም በገበያ ላይ ሰፊ አቅርቦትና ውድድር ሊኖር የሚችልበትን ጊዜ ታሳቢ በማድረግ የግዥ መፈጸሚያ ጊዜን ሊወስን እንደሚገባ የማሻሻያ ሀሳብ ተሰጥቶ ነበር፡፡

90. አገልግሎቱ ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት በደብዳቤ ቁጥር ግንማ 14/1/12/8265 ጥር 18 ቀን 2007 ዓ.ም. አዘጋጅቶ በላከው የድርጊት መርሃ-ግብር ግዥውን በወቅቱ በመፈጸም መ/ቤቶች በበጀታቸው እንዲጠቀሙ እንደሚያደርግ ገልጿል፡፡

91. የክትትል ኦዲት በተከናወነበት ወቅት የሚከተሉት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡-

92. አገልግሎቱ የማዕቀፍ ግዥ ጨረታ የሚያወጣው ዕቃዎችን ለማግኘት ብዙ ውድድር በሚኖርበት በመጋቢት ወር እንደሆነና ግዥው ከመ/ቤቶች ፕሮግራም/በጀት አመት ጋር የተጣጣመ መሆኑን፣ የግዥ ሂደት መጓተትን ለመቅረፍ የሦስት ዓመት ግዥን በአንድ ጊዜ እየተፈራረሙ ግዥ እየፈፀሙ እንደሆነና ይህም አሰራር ችግሩን የቀረፈ ቢሆንም በ2010 በጀት ዓመት በመንግስት ደረጃ በተደረገ የምንዛሬ ለውጥ ምክንያት አቅርቦቱ መስተጓጎሉን የአገልግሎቱ የሚመለከታቸው የሥራ ሀላፊዎች በቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ ገልፀዋል፡፡

93. የአገልግሎቱ የስራ ሃላፊዎች ይህን ይበሉ እንጅ የ2008-2010 ዓ.ም የግዥ ሂደት አጠናቆ ውል የተፈራረመው ህዳር፣ ታህሳስ፣ መጋቢትና ግንቦት 2008 ዓ.ም መሆኑና ይህም ማለት ከሁለተኛው ሩብ አመት እስከ አራተኛው ሩብ አመት ድረስ የግዥ ሂደት እንደነበር የሚያሳይ ስለሆነ ግዥው ከመ/ቤቶች የበጀት አመት /ፕሮግራም/ ጋር የተጣጣመ አለመሆኑ በአገልግሎቱ ከተከለሱ ማስረጃዎች ለማወቅ ተችሏል፡፡

94. በናሙና የታዩት የተለያዩ የፌዴራል መ/ቤቶች የሚፈልጉትን ዕቃዎችና አገልግሎቶች ግዥ ባስቀመጡት የግዥ መርሃ ግብር ማለትም የግዥ እቅዳቸውን በየሩብ ዓመት ከፋፍለው ለአገልግሎቱ የሚያሳውቁ ቢሆንም በታቀደው መሰረት እንደማያገኙና ወደ ቀጣዩ ሩብ ዓመትና በበጀት ዓመቱም እንደማይሳካ፣ በ2010 ዓ.ም ላይ ሙሉ በሙሉ ሳይገዙ የቀሩበት ሁኔታ እንዳለ በክትትል ኦዲቱ ወቅት በናሙና የታዩ ንግድ ሚኒስቴር፣ ትምህርት ሚኒስቴር፣ ማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ኤጀንሲ፣ የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስጣን፣ የኢትዮጵያ የደረጃዎች ኤጀንሲ፣ የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር እና አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የሚመለከታቸው የሥራ ሃላፊዎች ከቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ ለመረዳት ተችሏል

95. ስለጉዳዩ የሚመለከታቸው የአገልግሎቱ የበላይ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ:-

- መ/ቤቶች የግዥ ፍላጎታቸውን ዘግይተው ስለሚልኩና የግምገማ ሂደቱ በመዘግየቱ ምክንያት አገልግሎቱ ከ2008-2010 ዓ.ም ላለው የማዕቀፍ ግዥ የግዥ ሂደት አጠናቆ ህዳር፣ ታህሳስ፣ መጋቢትና ግንቦት 2008 ዓ.ም ውል እንዲፈራረም እንደተገደደ ገልጸዋል፡፡ ይህም ማለት የግዥ ሂደቱ

የተጠናቀቀው ከሁለተኛው እስከ አራተኛው ሩብ ዓመት ድረስ በመሆኑ ከባለበጀት መ/ቤቶች የበጀት ዓመት (ፕሮግራም) ጋር ሊጣጣም እንዳልቻለ ታውቋል፤

- በ2010 ዓ.ም በውጭ ምንዛሪ እጥረት ምክንያት አቅራቢዎች ዋጋ አስተካክሉ በማለት ዕቃ አለማቅረባቸው እና በወቅቱ የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ የገበያ ጥናት ያልነበረው በመሆኑ ምክንያት አገልግሎቱ የዋጋ ማስተካከያ ማድረግ እንዳልቻሉ ገልጸዋል፤

96.የአገልግሎቱ የበላይ ኃላፊዎች ይህን ይበሉ እንጂ የግዥ ሂደት ከመንግሥት መ/ቤቶች ከ2008-2010 በጀት ዓመት መጣጣሙን በተመለከተ ተጠይቀው በሰጡት መልስ የመንግሥት መ/ቤቶች የግዥ ፍላጎታቸውን በወቅቱ ከላኩ ግዥ በወቅቱ እንደሚፈጸምና አገልግሎቱ በበጀት አመቱ የሚፈጽማቸውን ዕቃዎች ዝርዝር በወቅቱ ለመ/ቤቶች እንደሚልክ፣ እንዲሁም በዝርዝር ውስጥ የሌሉትንም መ/ቤቶች የመንግሥት ግዥ ሥርዓት ጠብቀው እንዲገዙ በወቅቱ መገለጹን እና በ2008 ዓ.ም. የግዥ ፍላጎት እንዲልኩ ከተጠየቁ 142 የፌዴራል መ/ቤቶች ውስጥ 52ቱ በወቅቱ እንዳላኩ እና ከ35 የመንግስት ዩኒቨርስቲዎች ውስጥ በወቅቱ የላኩት 18ቱ ብቻ በመሆናቸው የግዥ ፍላጎት ማሰባሰብ ረዘም ያለ ጊዜ እንደወሰደና ወደ ጨረታም ከተገባ በኋላ የቴክኒክ ግምገማ ለማድረግ ሰፊ ጊዜ በመውሰዱ የተነሳ ግዥው በታቀደው ጊዜ እንዳልተጠናቀቀ ገልጸዋል፡፡

አገልግሎቱ የጨረታ ሠነድ ሥራ ላይ ከመዋሉ በፊት በግዥ አፅዳቂ ኮሚቴ ተቀባይነት <u>ማግኘቱን ስለማረጋገጡ በተመለከተ፤</u>

97. በክዋኔ ኦዲቱ ወቅት የተገኘው፤

98. አገልግሎቱ ከ2003-2005 ዓ.ም. በግዥ አፅዳቂ ኮሚቴ ውሳኔ መሰረት ለሚፈፀም በጋራ ለሚፈለጉ ዕቃዎችና አገልግሎቶች ግዥ የሚዘጋጅ የጨረታ ሠነድ ሥራ ላይ ከመዋሉ በፊት ተቀባይነት ማግኘቱ በግዥ አጽዳቂ ኮሚቴ እንደማይረጋገጥ ተገኝቶ ነበር፡፡

99. በአገልግሎቱ የግዥ አፈፃፀም ሂደት ውስጥ በአዋጁ፣ በግዥ አፈፃፀም መመሪያ፣ ደንብና በኤጀንሲው በሚወጡ የአፈፃፀም ስርዓቶች መፈፀሙን ለማረጋገጥ እንዲያስችል በግዥ አፅዳቂ ኮሚቴ ውሳኔ መሰረት ለሚፈፀም በጋራ ለሚፈለጉ ዕቃዎችና አገልግሎቶች ግዥ የሚዘጋጅ ማንኛውም የጨረታ ሠነድ ሥራ ላይ

ከመዋሉ በፊት የግዥ አጽዳቂ ኮሚቴ በማቋቋም በኮሚቴው ተቀባይነት ማግኘቱ ሊረጋገጥ በተጨማሪም ከ10 ሚሊዮን ብር በላይ የሆኑ ዕቃዎችን በአለም አቀፍ ግዥ ጨረታ ግዥ ሊፈጽም ይገባል የሚል የማሻሻያ ሀሳብ ተሰጥቶ ነበር፡፡

100. አገልግሎቱ ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት በደብዳቤ ቁጥር ግንማ 14/1/12/8265 ጥር 18 ቀን 2007 ዓ.ም. አዘጋጅቶ በላከው የድርጊት መርሃ-ግብር የጨረታ ሰነዶች የሚጸድቁት ከመቶ ሚሊዮን በታች ባጽዳቂ ኮሚቴ ሲሆን ከመቶ ሚሊዮን ብር በላይ ሲሆን በግዥ አጽዳቂ ኮሚቴ ገምግሞ ለስራ አመራር ቦርድ እንዲጸድቅ የውሳኔ ሀሳብ በማቅረብ እንደሚያጸድቅ እና ከብር ከ10,000,000 ብር በላይ ዋጋ ያላቸው የጋራ መጠቀሚያ ዕቃዎች ግዥ በዓለም ዓቀፍ ግልፅ ጨረታ እንደሚያከናውን ገልጿል፡፡

101. የክትትል ኦዲት በተከናወነበት ወቅት የሚከተሉት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡-

102. በአገልግሎቱ ለሚፈፀሙ በጋራ ለሚፈለጉ ዕቃዎችና አገልግሎቶች ግዥ የሚውል የጨረታ ሰነድ ጨረታ ከመውጣቱ በፊት በአገልግሎቱ የግዥ አፅዳቂ ኮሚቴ እየፀደቀ መሆኑ እና ከ10,000,000 ብር በላይ ዋጋ ያላቸው የጋራ መጠቀሚያ ዕቃዎች ግዥ በዓለም ዓቀፍ ግልፅ ጨረታ እያከናወነ መሆኑ በክትትል ኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎች ለማወቅ ተችሏል፤

<u>አገልግሎቱ የተጫራቾችን ብቃት እና የስራ አፈፃፀማቸውን ማረጋገጡን በተመለከተ፤</u>

103. በክዋኔ ኦዲቱ ወቅት የተገኘው፤

104. አገልግሎቱ እጩ ተጫራቾች የግዥ ውልን ከመፈራረማቸው በፊት ውሉን መፈጸም የሚያስችል ብቃት እንዳላቸው ወጥ በሆነ መልኩ በጨረታ ሰነዱ ላይ በተቀመጠው የመገምገሚያ መስፈርት መሰረት የቅድመ ቴክኒክና ዝርዝር የቴክኒክ ግምገማ (prelimenarey and technical evaluation) ተደርጎ መረጋጋጡ መረጃ ተጠይቆ የተሟላ መረጃ ሊቀርብ አለመቻሉ ተገኝቶ ነበር፡፡

105. የመንግስት መ/ቤቶች የግዥ ውል ተፈፃሚ እንዲሆን በተቀመጠው ጊዜ ከአቅራቢ ድርጅቶች ዕቃ እንዲያገኙ ለማድረግ እንዲረዳ አገልግሎቱ በግዥ መመሪያውና በጨረታ ሰነዱ ላይ በተቀመጠው የመመዘኛ መስፈርት መሰረት ብቃታቸውን ሊያረጋግጥ፣ ቀደም ባሉ ጊዜያት ለመ/ቤቶች ዕቃና አገልግሎት ያቀርቡ የነበሩ አቅራቢ ድርጅቶች በድጋሚ ለመወዳደር በግዥ ጨረታ ላይ እጩ ተወዳዳሪ ሆነው ሲቀርቡ በፊት የነበራቸው የሥራ አፈጻጸም እንደ አንድ መገምገሚያ መሥፈርት ሆኖ ሊታይ ይገባል የሚል የማሻሻያ ሀሳብ ተሰጥቶ ነበር፡

106. አገልግሎቱ ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት በደብዳቤ ቁጥር ግንማ 14/1/12/8265 ጥር 18 ቀን 2007 ዓ.ም. አዘጋጅቶ በላከው የድርጊት መርሃ-ግብር በጨረታ ሰነዱ መሰረት የቅድመ ቴክኒክ፣ የፋይናንሻል ግምገማ እና ከተስማሚነት ምዘና ድርጅት የፍተሻ ውጤት ለተጫራቾች በተሰጠው ኮድ መሰረት ዝርዝር ቴክኒክ ግምገማ ስለመደረጉ፣

107. እንዲሁም የተጫራቹን ስምና ኮድ ወይም በመ/ቤቱ ባለሙያዎች ተተርጉሞ ውጤቱ የተቀመጠበትን የሚገልፅ ማስረጃ ተደራጅቶ እንዲቀመጥ የራሱ የሆነ ባለሙያና ክፍል ለማደራጀት እና በጨረታ ሰነዱ የተቀመጡት መስፈርቶች ተጨማሪ መስፈርት ተብለው የተቀመጡ በመሆናቸው ለወደፊት እንደ ዋና መስፈርት ለመውሰድ እንደታቀደ፤ እንዲሁም በቴክኒክ ግምገማ ያላለፉ ተጫራቾች ወደ ፋይናንሽል ግምገማ ማለፍ የማይችሉ መሆኑ እና የበፊት አፈጻጸማቸውን ግምት ውስጥ በማስገባት እንደሚሰሩ ገልጿል፡፡

108. የክትትል ኦዲት በተከናወነበት ወቅት የሚከተሉት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡-

109. አንድ አቅራቢ ድርጅት በቴክኒክ ግምገማ ውድቅ ከተደረገ በኋላ ቅሬታ አቅርቦ ቅሬታው ተቀባይነት ካላገኘ ወደ ፋይናንሻል ግምገማ እንደማያልፍ ነገርግን በግምገማው ወቅት ነባር የዕቃና አገልግሎት አቅራቢ ድርጅቶች በድጋሚ ለመወዳደር የበፊት የሥራ አፈጻጸማቸው እንደመገምገሚያ መስፈርት እንደማይታይ ማለትም በጊዜ ከማቅረብ አንጻር በመንግስት መ/ቤቶች ቅሬታ የቀረበባቸው አቅራቢ ድርጅቶች ይህንን ግድፈታቸው ታሳቢ ሳይደረግ በሚቀጥለው ዓመትም እንዳይሳተፉ የሚከለክል መስፈርት ሳይዘጋጅ የመንግስት ግዥና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ እስካላገዳቸው ድረስ አገልግሎቱ እንደማይመለከተው የአገልግሎቱ የሚመለከታቸው የስራ ሃላፊዎች ከቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ ለማወቅ ተችሏል፡፡

110. በአገልግሎቱ ዕቃ በስቶር ሳይኖራቸው ተወዳድረው የሚያሸንፉ አቅራቢዎች መኖራቸው፣ ጨረታ አሸንፈው አቅርቦት ላይ ችግር የሚፈጥሩ አቅራቢ ድርጅቶች እንደገና ተመልሰው በግዥ ጨረታ ላይ የሚወዳደሩበት ሁኔታ እንዳለ ከአገልግሎቱ የ2008 ዓ.ም የስራ አመራር ቦርድ ቃለ-ጉባኤ ለመረዳት ተችሏል፡፡

111. ስለጉዳዩ የሚመለከታቸው የአገልግሎቱ የበላይ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ የአቅራቢ ድርጅቶች የባለፈው የስራ አፈጻጸማቸውን እንደመገምገሚያ መስፈርት ባለመወሰዱ ምክንያት አቅራቢዎቹ ድጋሚ በአቅርቦት እየተሳተፉ

መሆኑ ችግር እየፈጠረ እንደሚገኝ ነገር ግን ለወደፊት ከ2011-2013 የግዥ ጨረታ ጊዜ እንደ መስፈርት ተደርጎ የሚወሰድ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

አገልግሎቱ በአገር ውስጥ ጨረታ ጊዜ የክፍያ ሁኔታ ስለማመቻቸቱ እና አቤቱታዎችንና ቅሬታዎችን ተቀብሎ የእርምት እርምጃ መውሰዱን በተመለከተ፤

112. በክዋኔ ኦዲቱ ወቅት የተገኘው፤

113. የመንግስት ግዥና ንብረት ማስወገድ አገልግሎት ተጫራቾች አወዳድሮ ግዥ በመፈፀም ዕቃ መረከብ ያልጀመረ ከመሆኑም በላይ የመንግስት መ/ቤቶች ዕቃ እንዲረከቡ ባዘዘው መሰረት ዕቃ ለሚረከቡ የመንግስት መ/ቤቶች ዕቃ ከተረከቡ በኋላ ከ5 እስከ 10 ባሉት የስራ ቀናት ውስጥ አስፈላጊውን የክፍያ ሁኔታ ያላመቻቸ መሆኑ ተገኝቶ ነበር፡፡

114. የመንግሥት ንብረት ግዥና ማስወገድ አገልግሎት የአገልግሎት አሰጣጥ ሂደቱን ለማሻሻል እንዲረዳውና ግዥዎች ሳይዘገዩ በተቀላጠፈ ሁኔታ ለመፈጸም እንዲያስችል አገልግሎቱ የተገልጋዮችን ቅሬታዎች ተቀብሎ ከሁለት እስከ አስር ቀናት ምላሽ ሊሰጥ እና የእርምት እርምጃዎችን ተግባራዊ ሊያደርግ እንደሚገባ የማሻሻያ ሀሳብ ተሰጥቶ ነበር፡፡

115. አገልግሎቱ ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት በደብዳቤ ቁጥር ግንማ 14/1/12/8265 ጥር 18 ቀን 2007 ዓ.ም. አዘጋጅቶ በላከው የድርጊት መርሃ-ግብር አገልግሎቱ የመንግስት መ/ቤቶች እቃውን ከተረከቡ በኋላ ለአቅራቢ ድርጅቱ በውሉ መሰረት ከ5-10 ባሉት የስራ ቀናት ውስጥ ለአቅራቢ ድርጅቱ ክፍያውን እንዲፈፅሙ እንደሚያደርግና የተገልጋዮችን ቅሬታዎች ተቀብሎ ከሁለት እስከ አስር ቀናት ምላሽ ሊሰጥ እና የእርምት እርምጃዎችን እንደሚወስዱ ገልጿል፡፡

116. የክትትል ኦዲት በተከናወነበት ወቅት የሚከተሉት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡-

117. አገልግሎቱ የመንግስት መ/ቤቶች እቃውን ከተረከቡ በኋላ ለአቅራቢ ድርጅቱ በውሉ መሰረት ከ5-10 ባሉት የስራ ቀናት ውስጥ ክፍያውን እንዲፈፅሙ የሚያሳውቅ መሆኑና በወቅቱ ክፍያ የማይፈፅሙትን በመለየት እርምጃ እንዲወሰድባቸው ለገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚ/ር የሚያሳውቅ መሆኑ፣

118. ይህን በተመለከተ አገልግሎቱ የውሉ ኮፒ ለባለበጀት መ/ቤቶች እየላከ የሚገኝ ሲሆን ዕቃውንም በተላከው ውል ኮፒ መሠረት እንዲረከቡ በመግለፅ መ/ቤቶች እራሳቸው እቃው በስፔስፊኬሽኑ ስለመቅረቡ አረጋግጠው መስፈርቱን የማያሟላ

ሲኖር ሪፖርት እንዲያደርጉለት የሚጠይቅ አሰራር የተዘረጋ መሆኑ፣ ነገር ግን አገልግሎቱ በዕቃ እርክክብ ወቅት ዕቃውን በዝርዝር ፍላጎት መግለጫ መሰረት ስለመገዛቱና ለመ/ቤቶች ስለመድረሱ እንደማያረጋግጥ ከተከለሱ ማስረጃዎች ለማወቅ ተችሏል፡፡

119. አገልግሎቱ ባለበጀት መ/ቤቶች ለሚያቀርቡት ቅሬታ ሀሳብ ከመስጠት ባለፈ አቅራቢዎች በውለታው መሰረት ዕቃ ስለማቅረባቸው ወጥ በሆነ መልኩ ቼክሊስት አዘጋጅቶ እንደማይከታተል በክትትል ኦዲቱ ወቅት በናሙና የታዩት ባለበጀት መ/ቤቶች፡- ንግድ ሚኒስቴር፣ ትምህርት ሚኒስቴር፣ ማዕከላዊ ስታቲስቲክስ፣ የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስጣን፣ የኢትዮጵያ የደረጃዎች ኤጀንሲ፣ የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር እና አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የሚመለከታቸው የስራ ሀላፊዎች በቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ ገልፀዋል፡፡

120. ስለጉዳዩ የሚመለከታቸው የአገልግሎቱ የበላይ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ አገልግሎቱ ሁሉንም ባለበጀት መ/ቤቶችና የመንግስት ዩኒቨርስቲዎች የተገዛላቸውን እቃ ሄዶ ማረጋገጥ አስቸጋሪ ስለሆነ ዕቃውን በተላከላቸው ዝርዝር ፍላጎት መግለጫ መሰረት እቃውን እንዲረከቡ የሚያደርግ መሆኑና አገልግሎቱ እቃውን ስለመረከባቸው በናሙና በተመረጡ መ/ቤቶች ላይ የማረጋገጥ ስራ እየሰራ መሆኑን ገልጸዋል፤

121. ይሁን እንጂ መ/ቤቶች ዕቃ እንዲረከቡና እቃው በስፔስፊኬሽኑ ስለመቅረቡ አረጋግጠው እንዲወስዱ በተለያየ ቀን ደብዳቤ መተላለፉ ቢታወቅም በግዥና ውል አስተዳደር መመሪያ ላይ አገልግሎቱ ለመ/ቤቶች የተገዙትን ዕቃዎች በሚፈለገው ስፔስፊኬሽን መሰረት መቅረቡን ሊመረምር፣ ወይም በባለሙያ አስፈላጊው ምርመራ እንዲደረግ ሁኔታዎችን ሊያመቻችና ከምርመራ በኋላ አስፈላጊውን የዕቃ ርክክብ እንዲፈፀም ቢገለጽም አገልግሎቱ ይህን ተግባር አለመፈጸሙ ተገቢ ሆኖ አላገኘነውም፤

አገልግሎቱ የሚፈራረማቸው የግዥ ውሎች የተሟላ መረጃ /መመሪያ መያዛቸው፣ ተግባራዊ መደረጋቸውን በተመለከተ ስለመከታተሉ እና ለመንግስት መ/ቤቶች በግዥ ዙሪያ ድጋፍ ስለማድረጉ፤

122. በክዋኔ ኦዲቱ ወቅት የተገኘው፤

123. አገልግሎቱ በ2004ና 2005 ዓ.ም ከአቅራቢ ድርጅቶች ጋር በተደረገው የማዕቀፍ ግዥ ስምምነት ውል ላይ ዕቃውን የሚገዙ ወይም የሚረከቡ የመንግስት መ/ቤቶች ዝርዝር እንዲሁም ክትትልና ግምገማ የሚደረግበትን ሥርዓት ያላካተተ መሆኑ፣ በዚህ ዙሪያ በናሙና ከታዩ 5 ዕቃ አቅራቢ ድርጅቶች ውስጥ ለ2005 በጀት ዓመት ግዥ ለስናፕ ትሬድንግ እና ለኤም ኤፍ አይ ኦፍስ ሶሉሽን አገልግሎቱ የመ/ቤቶችን ዝርዝር ውሉን ከተፈራረመ ከ2 ወር በኋላ ቢያሳውቃቸውም ከ2003-2005 ዓ.ም. በተፈፀመው የግዥ ውል ላይ የመንግሥት መ/ቤቶች ዝርዝር በወቅቱ ባለመካተታቸው 5ቱም የዕቃ አቅራቢ ድርጅቶች ለስንትና ለየትኞቹ መ/ቤቶች ዕቃ ማቅረብ እንዳለባቸው ቀድመው እንዳያቅዱ ያደረጋቸው መሆኑ ተገኝቶ ነበር፡፡

124. ከግዥው ዓላማ አንፃር የመንግስት መ/ቤቶች የሚያጠፉትን ጊዜ ለመቆጠብ እንዲረዳ አገልግሎቱ የሚፈራረመው የማዕቀፍ ግዥ ስምምነት ውል ላይ የአቅራቢው ኃላፊነትና ግዴታ፣ የመንግስት መ/ቤቶች ዝርዝር፣ የግዢ ትዕዛዝ የሚተላለፍበትን፣ ርክክብና ክፍያ የሚፈፀምበትን፣

125. እንዲሁም ክትትልና ግምምገማ የሚደረግበትን ሥርዓት ሊያካትትና ተግባራዊ ሊያደርግ፣ የማዕቀፍ ስምምነት አቅራቢው ድርጅት በውሉና በውሉ ላይ በተቀመጠው ግዴታ መሰረት እየፈፀመ መሆኑን ሊከታተል እና ለመንግስት መ/ቤቶች በግዥ ዙሪያ ድጋፍ ሊያደርግ እንዲሁም አቅራቢዎች የውል ማስከበሪያ ብለው የሚያስይዙትን ገንዘብ በውሉ መሰረት መፈፀማቸውን የሚያረጋግጥበት ሥርዓት ሊኖረውና በውሉ መሰረት እንዳልፈፀሙ ሲያውቅ ገንዙቡን ሊወርስ ይገባል የሚል የማሻሻያ ሀሳብ ተሰጥቶ ነበር፡፡

126. አገልግሎቱ ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት በደብዳቤ ቁጥር ግንማ 14/1/12/8265 ጥር 18 ቀን 2007 ዓ.ም. አዘጋጅቶ በላከው የድርጊት መርሃ-ግብር የማዕቀፍ ግዥ ስምምነት ውል ላይ ዕቃውን የሚገዙ ወይም የሚረከቡ የመንግስት መ/ቤቶች ዝርዝር እንዲሁም ክትትልና ግምገማ የሚደረግበትን ሥርዓትና አቅራቢ

ድርጅቶች በውሉ መሰረት እየፈጸሙ መሆናቸውን የሚከታተልበት እና የውል ማስከበሪያ የሚወርስበት ስርዓት እንደሚዘረጋ ገልጿል፡፡

127. የክትትል ኦዲት በተከናወነበት ወቅት የሚከተሉት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡-

128. አገልግሎቱ ግዥውን በተመለከተ ዕቃ አቅራቢ ድርጅቶችንና መ/ቤቶችን አልፎ አልፎ የሚከታተል ቢሆንም ወጥ የሆነ (በመርሀ-ግር የተደገፈ) የክትትልና የቁጥጥር ሥርዓት ተግባራዊ አለማድረጉ እና መደበኛ በሆነ መልኩ ክትትል የሚያደርግበት ስርዓት ያልተቀመጠ መሆኑ፣

129. አገልግሎቱ አቅራቢዎች የውል ማስከበሪያ ብለው የሚያስይዙትን ገንዘብ በውሉ መሰረት መፈፀማቸውን የሚያረጋግጥበት ሥርዓት የዘረጋ ቢሆንም በውሉ መሰረት ያልፈጸሙ አቅራቢዎች ቢኖሩም የክትትል ኦዲቱ እስከተጠናቀቀበት ጊዜ ድረስ የውል ማስከበሪያውን ገንዘብ እንዳልወረሰ በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎችና ለሚመለከታቸው የስራ ሀላፊዎች በቀረበ ቃለ መጠይቅ ለማወቅ ተችሏል፡፡

130. ስለጉዳዩ የሚመለከታቸው የአገልግሎቱ የበላይ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ በአገልግሎቱ የተደራጀ ክፍልና ባለሙያ ባለመኖሩ እንዲሁም ከማዕከላዊ ስታስቲክስ ኤጀንሲ የገበያ ዋጋ መረጃ ባለመገኘቱ የዋጋ ማስተካከያ ያልተደረገላቸውን አቅራቢዎች የውል ማስከበሪያ ቢወረስ አገልግሎቱ የዋጋ ማስተካከያ ስላላደረገ ማቅረብ እንዳልቻሉና እንደውሉ ያልፈጸመው አገልግሎቱ ነው በማለት ወደ ፍርድ ቤት ቢሄዱ እስከነኪሳራው ጠይቀው መንግስትን ለአላስፈላጊ ወጭ እንዳይዳርጉ በማለት የመንግስት ግዥና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲን እና የገንዘብ ሚኒስቴርን ሙያዊ ምክር እንዲሰጧቸው የጠየቁና ከሁለቱ መ/ቤቶች በሚሰጠው ሙያዊ ምክር መሰረት የሚፈጽሙ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

<u>አገልግሎቱ የሚፈራረማቸው የግዥ ውሎች የቴክኒክ ፍላጎት መግለጫ /Specification/ የያዙ መሆናቸውን እና በዛ መሰረት ግዥ መፈፀሙን በተመለከተ፤</u>

131. በክዋኔ ኦዲቱ ወቅት የተገኘው፤

132. በኦዲቱ ወቅት አገልግሎቱ በ2004ና በ2005 በጀት ዓመት የቴክኒክ ፍላጎት መግለጫ /Specification/ ባዘጋጀበት ጊዜ በተሟላ መልኩ የኢትዮጵያ ደረጃዎች ባለስልጣን ወይም እንደግዥው ዓይነት አግባብ ያላቸው ሌሎች አካላት የሚያወጧቸውን በጋራ የሚፈለጉ ተመሳሳይ ዕቃዎች ደረጃ በጨረታ ሰነዱ ላይ ስለዕቃው ደረጃ ዝርዝር አለመገለፁ፣ በዚህ ዙሪያ ከኢትዮጵያ ደረጃዎች ኤጀንሲና

አግባብ ካላቸው ከሚመለከታቸው አካላት ጋር የቴክኒክ ፍላጎት መግለጫን (specification) በተመለከተ ቅንጅታዊ አሰራር ስርዓት እንዳልዘረጋና ተግባራዊ እንዳላደረገ ተገኝቶ ነበር፡፡

133. ለመንግስት መ/ቤቶች የሚቀርቡ ዕቃዎች የጥራት ደረጃቸውን የጠበቁ እንዲሆኑ አገልግሎቱ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመወያየት ደረጃ ላልወጣላቸው ደረጃ እንዲዘጋጅ በማድረግ እንዲሁም ለሁሉም ዕቃ የመመሪመሪያ መሳሪያዎች እንዲኖሩ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመቀናጀት ሁኔታዎች እንዲመቻች በማድረግ በአቅራቢዎች የሚቀርቡ ዕቃዎች ሙሉ በሙሉ በታወቀ መ/ቤት የናሙና ፍተሻ እንዲደረግላቸው፣

134. በተጨማሪም የናሙና ፍተሻ በማስደረግ ብቻ ሳይሆን እቃ አቅራቢዎች ዘንድ አልፎ አልፎ በመሄድ የዕቃውን ጥራት በማረጋገጥ አገልግሎቱ ለመንግሥት መ/ቤቶች ጥራታቸውን የጠበቁ ዕቃዎችን በተመጣጣኝ ዋጋ ሊገዛና የመንግስት መ/ቤቶች በፌዴራል መንግስት በንብረት አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 9/2003 አንቀፅ 2 እና የገንዘብ ክፍያ መመሪያ ቁጥር 4/2003 አንቀፅ 9 መሰረት ከክፍያ በፊት ሊደረጉ የሚገባቸውና በዕቃ ርክክብ መወሰድ የሚገባቸውን ጥንቃቄ ለመውሰድእንዲ ያስችላቸው አገልግሎቱ ለመ/ቤቶች የተገዙትን ዕቃዎች በሚፈለገው ስፔስፊኬሽን መሰረት መቅረቡን ሊመረምር ወይም በባለሙያ አስፈላጊው ምርመራ እንዲደረግ ፣

135. አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ የራሱን ባለሙያ በመላክ ሁኔታዎችን ሊያመቻች እና ከምርመራ በኋላ የዕቃ ርክክብ እንዲፈፀም ሊያደርግ እንደሚገባ የማሻሻያ ሀሳብ ተሰጥቶ ነበር፡፡

136. አገልግሎቱ ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት በደብዳቤ ቁጥር ግንማ 14/1/12/8265 ጥር 18 ቀን 2007 ዓ.ም. አዘጋጅቶ በላከው የድርጊት መርሃ-ግብር በኢትዮጵያ የተስማሚነት ድርጅት ዕቃዎች እየተፈተሹ የተገዙ ቢሆንም ለወደፊት ከዚህ በበለጠ እንደሚሰሩ፣ ለመንግስት መ/ቤቶች የአቅራቢ ምደባ ሲያሳውቅ ስፔስፊኬሽኑን ከደብዳቤ ጋር አያይዞ እንደሚልክና ከዚህም ጋር በተያያዘ ችግር ሲገጥማቸው ለአገልግሎቱ እንዲያሳውቁ እንደሚያደርግ ገልጿል፡፡

137. የክትትል ኦዲት በተከናወነበት ወቅት የሚከተሉት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡-

138. አገልግሎቱ የመንግስት ግዥና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ በዕቃዎች ደረጃ ላይ ስልጠና ባዘጋጀበት ወቅት የሰጠውን የኢትዮጵያ ደረጃዎች ባለሥልጣን ያወጣውን የደረጃ ሰነድ እና የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ እቃዎችን በሚመለከት ከመገናኛ ኢንፎርሜሽን ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂ ሚ/ር በመውሰድ የቴክኒክ ፍላጎት መግለጫ በማዘጋጀት እንደሚጠቀሙ ነገር ግን ቅንጅታዊ አሰራርን በተመለከተ የስምምነት ሰነድ/MOU/ ከደረጃዎች ኤጀንሲ እና ከመገናኛ ኢንፎርሜሽን ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር እንዲሁም ከሌሎች ባለድርሻ አካለት ጋር እንዳልተፈራረመ የአገልግሎቱ የሚመለከታቸው የሥራ ሀላፊዎች በቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ ገልፀዋል፡፡

139. ከዚህ ቀደም በኢትዮጵያ ደረጃዎች ኤጀንሲ ደረጃ እንዲወጣላቸው ከተላኩት እቃዎች ውስጥ አሁንም 132ቱ ዕቃዎች ደረጃ ተዘጋጅቶ ያልጸደቀላቸው መሆኑ የአገልግሎቱ የሚመለከታቸው የሥራ ሀላፊዎች ከቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ ለማወቅ ተችሏል፡፡

140. አገልግሎቱ ጎማዎችን በሚመለከት ከአንበሳ አውቶብስ ድርጅት እንዲፈተሽ የጠየቀበት ሁኔታ ቢኖርም በመፈተሻ ማሽን እጥረት ምክንያት ፍተሻው አለመከናወኑና ይህን ፍተሻ ለማከናወን ሌላ አማራጭ አለመጠቀሙ፣ በ2007 ዓ.ም የአዲስ አበባ ከተማ አንበሳ አውቶብስ ድርጅት ጎማ የገመገመ ቢሆንም በ2008 ዓ.ም ድርጅቱ ፈቃደኛ ባለመሆኑ የጎማ ቴክኒክ ግምገማ እንዳልተደረገ ከአገልግሎቱ የማኔጅመንት ቃለ ጉባኤ ታውቋል፡፡

141. በኢትዮጵያ የተስማሚነት ምዘና ድርጅት በመፈተሻ መሳሪያ እጥረት ምክንያት መፈተሽ ያልተቻሉትን እቃወች እንደ ቶነር፣ ካርትሪጅና የመሳሰሉትን እቃዎች ከሌሎች አካላት ጋር በመተባበር መፈተሽ የሚቻልበትን ሁኔታ እንዳላመቻቸ ከተከለሱ ማስረጃዎች ለማወቅ ተችሏል፡፡

142. አገልግሎቱ በአገር ውስጥ ጨረታ ጊዜ በዕቃ እርክክብ ወቅት ዕቃውን በዝርዝር ፍላጎት መግለጫ መሰረት ስለመገዛቱና ለመ/ቤቶች ስለመድረሱ የማያረጋግጥ መሆኑን በክትትል ኦዲቱ ወቅት በናሙና የታዩት ባለበጀት መ/ቤቶች ንግድ ሚኔስቴር፣ ትምህርት ሚኒስቴር፣ ማዕከላዊ ስታቲስቲክስ፣ የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስጣን፣ የኢትዮጵያ የደረጃዎች ኤጀንሲ፣ የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር እና አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የስራ ሀላፊዎች በቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ ገልፀዋል፡፡

143. ስለጉዳዩ የሚመለከታቸው የአገልግሎቱ የበላይ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ፡-

- አገልግሎቱ ከባለድርሻ አካላት ጋር በጋራ ለመስራት ተነሳሽነት ባለመኖር እና ሁሉም በየግሉ ስራን ለማከናወን ስለሚሯሯጥ ከደረጃዎች ኤጀንሲ እና ከመገናኛ ኢንፎርሜሽን ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር ጋር የጋራ የመግባቢያ ስምምነት ሰነድ እንዳልተፈራረመ ገልጸዋል፡፡
- ደረጃ ያልወጣላቸው እቃዎች ደረጃ እንዲወጣላቸው ማድረግ የመንግስት ግዥና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ ሃላፊነት በመሆኑ ምክንያት በኢትዮጵያ ደረጃዎች ኤጀንሲ ደረጃ እንዲወጣላቸው ከተላኩት እቃዎች ውስጥ አሁንም ለ132ቱ ዕቃዎች ደረጃ ተዘጋጅቶ ስለመጽደቁ ወይንም ስላለመጽደቁ የአገልግሎቱ ሀላፊዎች የሚያውቁት ነገር እንደሌለ ገልጸዋል፡፡

144. ስለጉዳዩ የሚመለከታቸው የመንግስት ግዥና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ የበላይ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ መቶ ሰላሳ ሁለቱ (132ቱ) ዕቃዎች የተባሉት ማለትም ኮምፒዩተርና አክሰሰሪ፣ የጽዳት ዕቃዎች፣ የመኪና ጎማዎችና የመሳሰሉት በተፈጥሯቸው የተለዋዋጭነት ባህሪ ስላላቸው ደረጃ ሊወጣላቸው እንደማይችል ስለታመነበት መሆኑን ገልጸዋል፡

145. የኤጀንሲው የበላይ ሀላፊዎች ይህን ይበሉ እንጂ በተፈጥሯቸው ተለዋዋጭ የሆኑት እቃዎች ደረጃቸውን ለማውጣት አስቸጋሪ መሆኑና ደረጃ እንዲወጣላቸው ግዴታ እንደሌለው የተገለፀበት ህጋዊ ማስረጃ ባለመቅረቡ ለመቀበል ያስቸግራል፡፡

አገልግሎቱ የሚፈራረመው የግዥ ውል የገበያ ጥናትና መረጃን የተመረኮዘ መሆኑን

<u>በተመለከተ፤</u>

146. በክዋኔ ኦዲቱ ወቅት የተገኘው፤

147. የመንግሥት ግዥና ንብረት ማስወገድ አልግሎት ለአብዛኛዎቹ የመንግሥት ባለበጀት መ/ቤቶች የማዕቀፍ ግዥ ውል ስምምነት ከመፈጸም ውጭ በወቅታዊ የገበያ መረጃ ላይ የተመሰረተ የግዥ አገልግሎት አለመስጠቱ፣ ከ2004-2005 ዓ.ም ለማዕቀፍ ስምምነት ግዥ የተፈራረመውን የዕቃዎች ውል ዋጋ በገበያ ጥናት ላይ ተመርኩዞ አለመወሰኑ፣ በመንግስት መ/ቤቶች በጋራ የሚፈለጉ የማዕቀፍ ግዥ ሲፈፀም የቀረበው ዋጋ መጋነኑንና አለመጋነኑን የሚገልፅ የዋጋ ጥናት ሣይደረግበት ግዥ የተፈጸመ መሆኑ፣

148. በአገልግሎቱም የተደራጀ የገበያ ጥናት ቡድን የሌለ መሆኑ እና የመንግስት መ/ቤቶች (ጠቅላይ ፍርድ ቤት፣ ጅማና አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲዎች) ዕቃዎችን በዝቅተኛ ወይም በተሻለ ዋጋ ቢያገኙም እንኳ የገበያ ጥናት ባለመጠናቱ ምክንያት አገልግሎቱ ግዥ እንዳይፈፅሙ የኤጀንሲውን ፍቃድ መጠየቅ እንዳለባቸው እንደሚያዝና ኤጀንሲውም የከለከላቸው መሆኑ ተገኝቶ ነበር፡፡

149. በመንግስት የግዥ አፈፃፀም መመሪያ ላይ በተሰጣቸው ኃላፊነት መሰረት ማዕከላዊ ስታትስቲክስ ኤጀንሲና የግዥና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ በመንግስት መ/ቤቶች በጋራ የሚፈልጉ ዕቃዎችና አገልግሎቶች ዝርዝር ላይ ወቅታዊ የሆነ የገበያ ጥናትና ለዋጋ ማስተካከያ የሚውል ጠቋሚ ዋጋ /price index/ አጥንተው እንዲሰጧቸው በመጠየቅ ወይም በድህረ ገፃቸው ላይ እንዲለቁ ለበላይ አካል በማሳወቅ አገልግሎቱ ለማዕቀፍ ግዥ የሚፈራረመውን የውል ዓይነትና ዋጋ፣

150. አገልግሎቱ ጥያቄ ሲቀርብለት ለመንግስት መ/ቤቶች፣ ለመንግስት የልማት ድርጅቶች፣ ለክልል መንግስታትና ለግሉ ዘርፍ የሚፈፅመውን ግዥ፣ ለግዥው የተመደበው በጀትና የግዥው መጠን መመጣጠኑን በማረጋገጥ፣ በጨረታ ሰነዱ ላይ የተመለከተውን የግገር የዋጋ ለውጥ ማስተካከያዎችን ሲያደርግ በወቅታዊ የገበያ መረጃ ላይ የተመሰረተ ሊሆን እንደሚገባ የማሻሻያ ሀሳብ ተሰጥቶ ነበር፡፡

151. አገልግሎቱ ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት በደብዳቤ ቁጥር ግንማ 14/1/12/8265 ጥር 18 ቀን 2007 ዓ.ም. አዘጋጅቶ በላከው የድርጊት መርሃ-ግብር ከ2006 በጀት ዓመት ጀምሮ የገበያ ዋጋ እየተጠና ግዥ እንደሚፈጸም ገልጿል፡፡

152. የክትትል ኦዲት በተከናወነበት ወቅት የሚከተሉት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡-

153. የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ኤጀንሲ በቀን 30 ጥቅምት 2010ዓ.ም የገበያ ጥናት ሲደረግ የንግድ ምልክት ሳይጠቅስ መረጃን መሰብሰብ በዋጋ ላይ ከፍተኛ ክፍተት እንደሚፈጥር ለአገልግሎቱ በሚልከው የችርቻሮ ዋጋ ጥናት ያሳወቀ ቢሆንም አገልግሎቱ ችላ በማለት ኤጀንሲው በሚልከው በችርቻሮ ዋጋ የዋጋ ማስተካከያና ጨረታ የሚያወጣ መሆኑ ከተከለሱ ማስረጃዎች ለማወቅ ተችሏል፡፡

154. አገልግሎቱ የዋጋ ማሻሻያ የሚያደርግ ቢሆንም አንዳንድ አቅራቢ ድርጅቶች ላይ ለምሳሌ፡- አባድር ሾፒንግ ላይ የሳሙና ዋጋ ተጨምሯል በሚል ዕቃው ለአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ እንደማያቀርብ ባሳወቀበት ወቅት ዩኒቨርሲቲው ለአገልግሎቱ ቢያሳውቅም አገልግሎቱ ራሱ ማጣራት የሚገባውን አቅራቢው የዋጋ

ጭማሪ ያደረገው የግዥ ትዕዛዝ ከተላለፈ በኋላ ወይስ በፊት የሚለውን ጉዳይ ለዩኒቨርሲቲው በማስተላለፉ ይህ ደግሞ ከግዥ ስምምነቱ አንፃር በዩኒቨርሲቲው ለማጣራት የሚያስቸግር በመሆኑ ምክንያት እስከመጨረሻው ባለመጣራቱ ግዥው ሳይፈፀም እንደቀረ የዩኒቨርሲቲው የሚሚለከታቸው የስራ ሃላፊዎች በቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ ገልፀዋል፡፡

155. አገልግሎቱ ከ2008-2010 ዓ.ም ለገዛቸው እቃዎች በማዕከላዊ ስታትስቲክስ ኤጀንሲ በሚያወጣው የችርቻሮ ዋጋ ጨረታ ወጥቶ ግዥ እየተከናወነ መሆኑና የገበያ ዋጋ ጥናት አሁን ላይ እየተሰራ ያለው ስራ መሰረታዊ መፍትሔ እያመጣ አለመሆኑ ከአገልግሎቱ የቦርድ ስብሰባ ቃለ ጉባኤ ለማወቅ ተችሏል፡፡

156. አገልግሎቱም የመንግስት መ/ቤቶችን በጀት የማይጠይቅ እና የግዥ ሂደቱንም የሚያካሂደው በመንግስት መ/ቤቶች በጀት መሆኑ፣ የመ/ቤቶች በጀት ስንት እንደሆነ እንደማያውቅና ከመ/ቤቶች የዕቃ ፍላጎት ጥያቄ በመነሳት ጨረታ እንደሚያወጣ የአገልግሎቱ የሚመለከታቸው የሥራ ሃላፊዎች ከቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ ታውቋል፡፡

157. አገልግሎቱ ለግዥው የተመደበውና የግዥው መጠን መመጣጠኑን ሊያረጋግጥ እንደሚገባ በውስጥ መመሪያ 02/2004ዓ.ም የተቀመጠ ቢሆንም የግዥ ገንዘብ ግምታዊ በጀት ማዘጋጀት የያንዳንዱ ባለበጀት መ/ቤት ኃላፊነት እንጂ የአገልግሎቱ ተግባር አለመሆኑን የአገልግሎቱ የስራ ሀላፊዎች በቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ ገልፀዋል፡፡

158. ስለጉዳዩ የሚመለከታቸው የአገልግሎቱ የበላይ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ፡-

- የንግድ ምልክት ጠቅሶ ጥናት ማከናወን ለአንድ ወገን ስለሚያደላ ምልክቱን ባለመጥቀስ መደረግ እንዳለበት ስለሚታመንና የችርቻሮና ጅምላ ዋጋ የሚል መመሪያው ላይ የተጠቀሰ ባለመኖሩ በዚህ አግባብ ጨረታ ወጥቶ ግዥው የተከናወነ መሆኑ ገልጸዋል፤
- አገልግሎቱ በውስጥ መመሪያ 02/2004 ዓ.ም ለግዥው የተመደበውና የግዥው መጠን መመጣጠኑን ማረጋገጥ ያልቻለበት መመሪያው ሲወጣ ወቅታዊ ሁኔታዎችን በተጨባጭ ያላገናዘበ በመሆኑ ምክንያት መሆኑና

ለወደፊት መመሪያው ያለው ነባራዊ ሁኔታ በማገናዘብ የሚሻሻል እንደሆነ ገልጸዋል፡፡

159. ይሁን እንጂ ከላይ እንደተገለጸው ለግዥው የተመደበውና የግዥው መጠን መመጣጠኑን ማረጋገጥ ያልተቻለበት መመሪያው ሲወጣ ወቅታዊ ሁኔታዎችን በተጨባጭ ያላገናዘበ በመሆኑ ምክንያት ቢሆንም ግን መመሪያው የክትትል ኦዲቱ እስከተጠናቀቀበት ጊዜ ድረስ ያልተሻሻለ መሆኑ አልተቀበልነውም፡፡

<u>አገልግሎቱ በጨረታ ሰነዱ ላይ ስለማስረከቢያ ቦታ፣ ጊዜ እንዲሁም የዋጋ ማስተካከያ ስለሚደረግበት ሁኔታ ያካተተ መሆኑን በተመለከተ፤</u>

160. በክዋኔ ኦዲቱ ወቅት የተገኘው፤

161. አገልግሎቱ የማዕቀፍ ስምምነት ግዥ ውል ተፈፃሚ መሆን ከጀመረበት ከ3ወር በኋላ ለሚኖር ግዢ የዋጋ ለውጥ ወይም ማስተካከያ ማድረግ እንደሚቻል በጨረታ ሰነዱ ላይ ቢያመላክትም የዕቃዎች የዋጋ ጥናት ባለመዘጋጀቱ ዋጋ ሲጨምር እና ሲቀንስ ለዕቃ አቅራቢ ድርጅቶችም ሆነ ለመንግስት መ/ቤቶች የዋጋ ለውጥ አለማድረጉ፣ በ2004 እና በ2005 ባወጣው የጨረታ ሰነድ ላይ የመንግሥት መ/ቤቶች ዝርዝርና ግምታዊ የማስረከቢያ ጊዜ ያላካተተ መሆኑ ተገኝቶ ነበር፡፡

162. የመንግስት ግዥና ንብረት ማስወገድ አገልግሎት ተጫራች ድርጅቶች የመንግሥት መ/ቤቶች ዝርዝርና ግምታዊ የማስረከቢያ ጊዜን በመረዳት አቅማቸውን አውቀው ለመጫረት እንዲያስችላቸውና በዕቃ አቅርቦት ጊዜ ለአገልግሎቱ የሚቀርብለትን አቤቱታና ቅሬታ ለመቀነስ እንዲረዳ አገልግሎቱ በሚዘጋጀው የጨረታ ሰነድ ውስጥ የሚገዛቸውን ዕቃዎችና የማዕቀፍ ስምምነት የሚጠቀሙ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶችን ዝርዝርና ግምታዊ የማስረከቢያ ጊዜ እንዲካተት ሊያደረግ ይገባል የሚል የማሻሻያ ሀሳብ ተሰጥቶ ነበር፡፡

163. አገልግሎቱ ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት በደብዳቤ ቁጥር ግንማ 14/1/12/8265 ጥር 18 ቀን 2007 ዓ.ም. አዘጋጅቶ በላከው የድርጊት መርሃ-ግብር በጨረታ ሰነዱ ላይ ስለማስረከቢያ ቦታ፣ ጊዜ እንዲሁም የዋጋ ማስተካከያ ስለሚደረግበት ሁኔታ በመረሃ ግብሩ አለመካተቱ፡፡

164. የክትትል ኦዲት በተከናወነበት ወቅት የሚከተሉት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡-

165. አገልግሎቱ የዋጋ ማስተካከያ እንደሚደረግ በቀረበለት ቃለ-መጠይቅ ቢገልፅም በክትትል ኦዲቱ በናሙና የታዩት መ/ቤቶች፡- ንግድ ሚኒስቴር፣ ትምህርት

ሚኒስቴር፣ ማዕከላዊ ስታቲስቲክስ፣ የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስጣን፣ የኢትዮጵያ የደረጃዎች ኤጀንሲ፣ የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር እና አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በዋጋ ጭማሪ ምክንያት የግዥው ሂደት እንደሚጓተትና አቅራቢዎችም አገልግሎቱ የዋጋ ማስተካከያ ስላላደረገ ነው የሚል ምላሽ እንደሚሰጣቸው የሚመለከታቸው የመንግስት መ/ቤቶች የሥራ ሃላፊዎች በቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ ገልፀዋል፡፡

166. ስለጉዳዩ የሚመለከታቸው የአገልግሎቱ የበላይ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ አገልግሎቱ ከ2008-2010 ለሚገዛቸው ዕቃዎች ላይ የዋጋ ማሻሻያ በሚያስፈልግ ጊዜ የዋጋ ማሻሻያ ለማድረግ እንዲቻል የገበያ ጥናት የሚያደርግ ቡድን በ2009 ዓ.ም የተቋቋመ ቢሆንም የገበያ ዋጋ መረጃ ከማዕከላዊ ስታስቲክስ ኤጀንሲ ባለመገኘቱ ምክንያት የዋጋ ማስተካከያ እንዳልተደረገ ገልጸዋል፡፡ ነገር ግን ለወደፊት ከ2011-2013 ለሚገዛቸው ዕቃዎች ላይ የዋጋ ማሻሻያ በሚያስፈልግ ጊዜ የዋጋ ማሻሻያ እንደሚያደርጉ ገልጸዋል፡፡

167. ይሁን እንጂ አገልግሎቱ ከማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ጋር በጋራ በመተባበር የዋጋ ጥናት ሰርተው የዋጋ ጭማሪ በሚከሰትበት ወቅት ማሻሻያ ማድረግ እንዳለበት ስለሚታመን እና ለባለፈው 2008-2010 ዓ.ም ለተፈፀመው ግዥ የዋጋ ጭማሪ ተከስቶ ማሻሻያ አለማድረጉ ተገቢ ሁኖ አልተገኘም፡፡

አገልግሎቱ ጥራታቸውን የጠበቁ ዕቃዎች በተመጣጣኝ ዋጋ መግዛቱን እና ጥቅል ግዥ በመፈፀም ኢኮኖሚያዊ ጥቅም ማስገኘቱን በተመለከተ፤

168. በክዋኔ ኦዲቱ ወቅት የተገኘው፤

169. በኦዲቱ ወቅት ከ2004-2005 ዓ.ም አገልግሎቱ በፈፀመው የግዥ ውል መሰረት በመንግስት መ/ቤቶች የተገዙ ዕቃዎች ጥራትን በተመለከተ በናሙና ከታዩት 15 መ/ቤቶች ውስጥ 10ሩና በሰርቨይ መጠይቅ ተልኮላቸው ከመለሱት መ/ቤቶች ውስጥ 4 መ/ቤቶች የጥራት ችግር የገጠማቸው መሆኑ፣

170. ከእነዚህም ውስጥ 6 መ/ቤቶች ከአቅራቢዎች የገዙት ዕቃዎች ማለትም የፎቶ ኮፒና የፕሪንተር ወረቀቶች፣ ቶነሮች፣ ፕሪንተሮችና የፋይል አቃፊ ጥራታቸው ዝቅ ያለ በመሆኑ መ/ቤቶቹ ለሚጠቀሙበት የፎቶ ኮፒ ማሽን ተስማሚ ያልሆነና ጥራቱን ያልጠበቀ ወረቀት እንዲያገኙ ያደረገ መሆኑና የሳሳ ስለሆነ ፎቶ ኮፒ ሲያደርጉ እና ጽሑፎች በሚታተሙበት ጊዜ ስለሚጨማደድ በጣም እየተቸገሩ ከመሆኑም በላይ በርካታ ወረቀቶች ተበላሽቶባቸው ለብክነት የተጋለጡ መሆኑ፣

171. በአገልግሎቱ የተገዙ ቶነሮች ኦሪጅናል ሳይሆኑ ሪፍል /በድጋሚ የተሞሉ/ ስለሆነ ማሽኖች በየጊዜው እየተበላሹ ለጥገና ከፍተኛ ወጪ እንዲወጣ ማድረጉን በተጨማሪም የፋይል አቃፊን በተመለከተ ሰነዶችን በመያዝ ለማቆየት የማይችል፣ በቀላሉ የሚቀደድና ለመገንጠልም የተጋለጠ ሲሆን ፕሪንተሮቹንም ያለአገልግሎት መቀመጣቸውን፣

172. የመንግስት ግዥና ንብረት ማስወገድ አገልግሎት ጥቅል ግዥ በመፈፀም ኢኮኖሚያዊ ጥቅም ማስገኘቱ ሲታይ የመንግስት መ/ቤቶች ከ2004 ዓ.ም. ጀምሮ በአገልግሎቱ በኩል ግዥ እንዲፈፅሙ ቢደረግም አገልግሎቱ ለመንግስት መ/ቤቶች ተመሳሳይ በጋራ የሚፈለጉ ዕቃዎች ጥቅል ግዢ በመፈፀም ያስገኘው የኢኮኖሚያዊ ጥቅም አለመኖሩ ተገኝቶ ነበር፡፡

173. በደንብ ቁጥር 184/2002 ላይ የተቀመጠውን የአገልግሎቱን ዓላማ ለማሳካት እንዲረዳ እና የመንግስት መ/ቤቶች ለቁጥቁጥ ግዢና ለዋጋ ንረት እንዳይጋለጡ ለመንግስት መ/ቤቶች ተመሳሳይ በጋራ የሚፈለጉ ዕቃዎችና አገልግሎቶች ጥቅል ግዢ በመፈፀም ለሀገሪቱ ኢኮኖሚያዊ ጥቅም ሊያስገኝ እና ያስገኘው የኢኮኖሚ ጥቅም ሊታወቅ ይገባል የሚል የማሻሻያ ሀሳብ ተሰጥቶ ነበር፡፡

174. አገልግሎቱ ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት በደብዳቤ ቁጥር ግንማ 14/1/12/8265 ጥር 18 ቀን 2007 ዓ.ም. አዘጋጅቶ በላከው የድርጊት መርሃ-ግብር በአቅራቢዎች ላይ ጥብቅ ቁጥጥር በማድረግ ችግሩን እንደሚቀረፍ እና ከ2007 በጀት ዓመት ጀምሮ በየአመቱ የተገኙ ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ እንደሚጠና ገልጿል፡፡

175. የክትትል ኦዲት በተከናወነበት ወቅት የሚከተሉት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡-

176. ለፌዴራል ባለበጀት መ/ቤቶች እና ዩኒቨርሲቲዎች የሚቀርቡ ፕሪንተርና ቶነር ዕቃ ጥራት ላይ ቅሬታ እንዳቀረቡ ከአገልግሎቱ የስራ አመራር ቦርድ ቃለ ጉባኤ ለማወቅ ተችሏል፡፡

177. አገልግሎቱ ለባለበጀት የመንግስት መ/ቤቶች በጋራ የሚፈለጉ ተመሳሳይ ዕቃዎችና አገልግሎቶች ጥቅል ግዥ በመፈጸሙ ያስገኘው የኢኮኖሚያዊ ጥቅም በየጊዜው ጥናት እያካሄደ እንደሆነ የአገልግሎቱ የሚመለከታቸው የስራ ሀላፊዎች በቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ የገለፁ ቢሆንም የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚ/ር ጥናቱ በገለልተኛ አካል እንዲጠና በወሰነው መሠረት ለመንግስት ግዥና ንብረት

አስተዳደር ኤጀንሲ ጥናቱን እንዲያካሂድ ሃላፊነት ተሰጥቶታል ቢባልም ሀላፊነቱ የተላለፈበት ማስረጃ እና በገለልተኛ ወገን የተጠና ጥናት የክትትል ኦዲቱ እስከተጠናቀቀበት ጊዜ አልቀረበም፡፡

178. ስለጉዳዩ የሚመለከታቸው የአገልግሎቱ የበላይ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ አገልግሎቱ ለባለበጀት የመንግስት መ/ቤቶች በጋራ የሚፈለጉ ተመሳሳይ ዕቃዎችና አገልግሎቶች ጥቅል ግዥ በመፈጸሙ ያስገኘው የኢኮኖሚያዊ ጥቅም የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚ/ር ጥናቱ በገለልተኛ አካል እንዲጠና በወሰነው መሠረት ለመንግስት ግዥና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ በየጊዜው ጥናት እንዲያካሂድ ሃላፊነት እንደሰጠው እና ጥናት ስለማድረጉ እውቅና እንደሌላቸው ገልጸዋል፡፡

179. ስለጉዳዩ የሚመለከታቸው የመንግስት ግዥና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ የበላይ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ የጥናቱ ሀላፊነት የኤጀንሲው እንደሆነ አምነው ነገር ግን እስከ 2010 መጨረሻ ተግባራዊ እንዳልተደረገ ነገር ግን 2011 ሁለተኛው ሩብ ዓመት አካባቢ ቢጋር (TOR) ተዘጋጅቶ የዩኒቨርሲቲዎች ምሁራኖች በተሳተፉበት ሁኔታ በሂደት ላይ እንደሚገኝ ገልጸዋል፡፡

አገልግሎቱ ከሌሎች አካላት ጋር የመረጃ ልውውጥ ስርዓት ስለመዘርጋቱ እና ግንዛቤ <u>መፍጠሩን በተመለከተ፤</u>

180. በክዋኔ ኦዲቱ ወቅት የተገኘው፤

181. አገልግሎቱ የግዥ ዕቅዶች፣ ሪፖርቶች፣ መመሪያዎችንና የግዥ መረጃዎችን ለመለዋወጥ የሚረዳ የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጅ ሲስተም ስርዓት ለመዘርጋት ቢያቅድም እስከ 2005 ዓ.ም ተግባራዊ በማድረግ ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር፣ ለመንግስት ግዥና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ፣ ለመንግስት መ/ቤቶችና ለአቅራቢ ድርጅቶች በወቅቱ መረጃዎች እንዲደርሱ አለማድረጉ፣

182. የመንግስት መ/ቤቶች በጋራ የሚፈለጉ ተመሳሳይ ዕቃዎችና አገልግሎቶች የማዕቀፍ ስምምነት ግዥ ዙሪያ ለባለድርሻ አካላት በመገናኛ ብዙሃን፣ በስብሰባ፣ በሴሚናር፣ በወርክሾፕ፣ በደብዳቤና በመወያያ መድረኮች ወዘተ ግንዛቤ እንዳልፈጠረላቸው ተገኝቶ ነበር፡፡

183. መ/ቤቶች የግዥ መረጃዎችን በወቅቱ ለመለዋወጥ እንዲረዳቸውና በየጊዜው የሚታዩ ችግሮችን ከመረጃ ላይ አይተው የመፍትሄ እርምጃ ለመውሰድ

እንዲያስችላቸው፣ የዕቃ አቅራቢ ድርጅቶችንና የመ/ቤታቸውን መብትና ግዴታ በማወቅ የግዥ ሂደቱ እንዳይጓተት ለማድረግ በፌዴራል መንግስት የግዥ አፈፃፀም መመሪያ ላይ በተገለፀው መሰረት እንደማንኛውም የመንግስት መ/ቤት የጨረታ አሸናፊው ከተመረጠና የግዥ ውል ከተፈራረመ በኃላ ባሉት 5 ቀናት ውስጥ በኤጀንሲው መረጃ መረብ ላይ አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎችን በመሙላት አገልግሎቱ ለህዝብ ይፋ እንዲደረግ ወይም የአገር ውስጥ ግዥ ሂደት አጠናቆ የማዕቀፍ ስምምነት በመፈራረም በወቅቱ የመንግስት ባለ በጀት መ/ቤቶች የግዥ ውሉን ኮፒ በመላክ እንዲያውቁት ሊያደርግ፣ ከባለድርሻ አካላት ጋር የተቀላጠፈ የመረጃ ልውውጥ እንዲኖረው በማድረግ እና የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጅ ሲስተም ስርዓት በመጠቀም የግዥ መረጃዎችን በወቅቱ ለባለድርሻ አካላት እንዲደርሱ ማድረግ እንዳለበት የማሻሻያ ሀሳብ ተሰጥቶ ነበር፡፡

184. አገልግሎቱ ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት በደብዳቤ ቁጥር ግንማ 14/1/12/8265 ጥር 18 ቀን 2007 ዓ.ም. አዘጋጅቶ በላከው የድርጊት መርሃ-ግብር ከአቅራቢዎች ጋር ውል ከተፈረመ በኋላ ፍላጎት ላቀረቡ መ/ቤቶች ምደባ እንደሚሰጣቸው፣ ነገር ግን ዘግይተው ጥያቄ ለሚያቀርቡ በ/ቤቶችም ምደባ እንደሚደረግ ገልጿል፡፡

185. የክትትል ኦዲት በተከናወነበት ወቅት የሚከተሉት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡-

186. አገልግሎቱ የራሱ የሆነ ዳታ ቤዝ ገንብቶ በጠቅላይ ሚኒስትሩ ጽ/ቤት በሚገኘው Government Portal ውስጥ እንዲካተት እየተደረገ መሆኑ፣ ሆኖም ግን መረጃን በቴክኖሎጂ አስደግፎ ማሰራጨትን በተመለከተ ክፍተት እነዳለ፣ የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጅ ስርዓትን ዘመናዊ የማድረግ ስራ እንዳልተጀመረ፣ ነገር ግን በቀጣይነት ዘመናዊ የማድረጉ ሥራ ትኩረት ተሰጥቶት የሚከናወን መሆኑን የአገልግሎቱ የሚመለከታቸው የስራ ሃላፊዎች ከቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ ለማወቅ ተችሏል፡፡

187. የመረጃ ልውውጥን በተመለከተ በደብዳቤ ብቻ እንጅ ዘመናዊ የመረጃ ልውውጥ ስርዓት እንደሌለ በክትትል ኦዲቱ በናሙና የታዩ መስሪያ ቤቶች በንግድ ሚኔስቴር ፣ ትምህርት ሚኒስቴር፣ ማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ኤጀንሲ፣ የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስጣን፣ የኢትዮጵያ የደረጃዎች ኤጀንሲ፣ የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር እና አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ ከአቅራቢዎች መካከል ናሽናል ማርኬተርስ፣ ራዲካል ኃ.የተ.የግ.ኩ ድርጅቶች የሚመለከታቸው የስራ ሀላፊዎች በቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ ገልፀዋል፡፡

188. ስለጉዳዩ የሚመለከታቸው የአገልግሎቱ የበላይ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ በአገልግሎቱ የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ስርዓትን ከማዘመን ረገድ የተደራጀ አካል ባለመኖሩና ሰራተኞች በየጊዜው በመልቀቃቸው ምክንያት ዘመናዊ የመረጃ ልውውጥ እንደሌለ ገልጸዋል፡፡

አገልግሎቱ የምክርና ስልጠና አገልግሎት ስለመስጠቱና እና የመወያያ መድረኮችን ማዘጋጀቱን በተመለከተ፤

189. በክዋኔ ኦዲቱ ወቅት የተገኘው፤

190. በኦዲቱ ወቅት በመስክ ምልከታ በታዩ 15 መ/ቤቶች እና የሰርቨይ መጠይቅ ከተላከላቸው 24 መ/ቤቶች ውስጥ ለ13ቱ (54%) ከ2003-2005 ዓ.ም አገልግሎቱ የግዥ አፈፃፀምን በተመለከተ ምክርና ስልጠና አለመስጠቱ እንዲሁም አገልግሎቱ በግዥ ሂደቱ የሚገጥሙትን ችግሮች ለመፍታት ከባለድርሻ አካላት ጋር መደበኛ የሆነ የመወያያ መድረኮችን በማዘጋጀት በተሟላ ሁኔታ ተቀናጅቶ ያልሰራ መሆኑ ተገኝቶ ነበር፡፡

191. የባለድርሻ አካላት ስለአገልግሎቱና ስለኤጀንሲው ልዩነት በአግባቡ እንዲያውቁና አገልግሎቶች ለመለየትና በጋራ የሚገዙ ዕቃዎች ከሚያስገኘው ጥቅም አንፃር እንዲሁም በሥራው ላይ የሚፈጠሩ ችግሮችን አስቀድሞ ለመቀነስና ችግሮች ሲፈጠሩ በቀላሉ ለመፍታት እንዲያስችል አገልግሎቱ መደበኛ የሆነ የመወያያ መድረኮችን በማዘጋጀት ከባለድርሻ አካላት ጋር ተቀናጅቶ ሊሰራ እንዲሁም የመንግስት መ/ቤቶች በጋራ የሚጠቀሙባቸው ተመሳሳይ ዕቃዎችና አገልግሎቶች የማዕቀፍ ስምምነት ግዥ ዙሪያ ለባለድርሻ አካላት የምክርና ሥልጠና አገልግሎት በመስጠት እና በመገናኛ ብዙሃን፣ በስብሰባ፣ በሴሚናር፣ በወርክሾፕ፣ በደብዳቤና በመወያያ መድረኮች ወዘተ ግንዛቤ ሊፈጥር እንደሚገባ የማሻሻያ ሀሳብ ተሰጥቶ ነበር፡፡

192. አገልግሎቱ ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት በደብዳቤ ቁጥር ግንማ 14/1/12/8265 ጥር 18 ቀን 2007 ዓ.ም. አዘጋጅቶ በላከው የድርጊት መርሃ-ግብር አገልግሎቱ የምክርና ስልጠና አገልግሎት ስለመስጠቱ እና የመወያያ መድረኮችን ማዘጋጀት በተመለከተ በመርሃ ግብሩ አላከተተም፡፡

193. የክትትል ኦዲት በተከናወነበት ወቅት የሚከተሉት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡-

194. አገልግሎቱ በግዥ ሂደቱ የሚያጋጥሙ ችግሮች ለመፍታት ከባለድርሻ አካላት ጋር በ2008ና 2009 በጀት ዓመት ወጥ የሆነ የመወያያ መድረኮችን በማመቻቸት የጋራ ምክክር መድረክ እንደሌለው ነገር ግን ከ2010 በጀት ዓመት ጀምሮ በየሩብ ዓመቱ መደበኛ የሆነ የመወያያ መድረኮችን በማመቻቸት የጋራ ምክክር የሚያደርግ ሲሆን የግዥ አፈፃፀምን በሚመለከት ለባለበጀት የመንግስት መ/ቤቶች የምክር አገልግሎት ድጋፍ እየሰጠ መሆኑ፣ አገልግሎቱ ስልጠናን በሚመለከት በራሱ እቅድ ይዞ ለተጠቃሚዎች ስልጠና እንደማይሰጡ የአገልግሎቱ የሚመለከታቸው የስራ ሃላፊዎች ከቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ ለማወቅ ተችሏል፡፡

195. አገልግሎቱ በመንግስት ግዥና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲና በመንግስት ግዥና ንብረት ማስወገድ አገልግሎት መካከል በተደረገው የትብብር ስምምነት ላይ ጥር 15/2005 ዓ.ም. በመንግስት ግዥና ንብረት ማስወገድ አገልግሎት ላይ የሚታዩትን ችግሮች በመለየት፣ ችግሮቹ የሚፈቱበትን አግባብ ውይይት ማቅረብ እና ግንዛቤ የመፍጠር ስራ መስራት እንዳለባቸው ቢቀመጥም ከስምምነቱ በፊትም ሆነ በኋላ በመደበኛነት የመወያያ መድረክ በማዘጋጀት በቅንጅት ያልሰራ መሆኑ እና ስምምነቱም እንደተቋረጠ የአገልግሎቱ የሚመለከታቸው ስራ ሃላፊዎች በቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ ገልፀዋል፡፡

196. አገልሎቱ ወጥ በሆነ መልኩ የውይይት መድረክ እንደማያዘጋጅ ነገር ግን አልፎ አልፎ እንደሚያከናውን እንዲሁም የምክርና ስልጠና ድጋፍ እንደማያደርግላቸው በክትትል ኦዲቱ በናሙና የታዩት መስሪያ ቤቶች ንግድ ሚኒስቴር፣ ትምህርት ሚኒስቴር፣ ማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ኤጀንሲ፣ የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን፣ የኢትዮጵያ የደረጃዎች ኤጀንሲ፣ የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር እና አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ የሚመለከታቸው የሥራ ሀላፊዎች ከቀረበላቸው ቃለ-መጠይቅ ለማወቅ ተችሏል፡፡

197. ስለጉዳዩ የሚመለከታቸው የአገልግሎቱ የበላይ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ፡-

- አገልግሎቱ የግዥ ስልጠና የሚሰጠው ጥያቄ ሲቀርብለት ብቻ መሆኑ ምክንያቱም ይህ ተግባር በዕቅድ ይዞ ስልጠና መስጠት የግዥና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲው ተግባር/ሀላፊነት በመሆኑ እንደሆን ገልጸዋል፡፡
- በኤጀንሲውና በአገልግሎቱ መካከል የተደረጉት የውይይቶች አጀንዳ ወደ አገልግሎቱ ስለሚያጋድሉ የኤጀንሲውን አስፈላጊነት ባለማየታቸው

ምክንያት በመንግስት ግዥና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲና በመንግስት ግዥና ንብረት ማስወገድ አገልግሎት መካከል ጥር 15/2005 ዓ.ም የተደረገው የትብብር ስምምነት ማለትም በመንግስት ግዥና ንብረት ማስወገድ አገልግሎት ላይ የሚታዩትን ችግሮች በመለየት፣ ችግሮቹ የሚፈቱበትን አግባብ ውይይት ማቅረብ እና ግንዛቤ የመፍጠር ስራ መስራት እንዳለባቸው ቢቀመጥም ከስምምነቱ በፊትም ሆነ በኋላ በመደበኛነት የመወያያ መድረክ በማዘጋጀት በቅንጅት ያልሰራ መሆኑ እና ስምምነቱም የተቋረጠ መሆኑ ገልጸዋል፡፡

198. ስለጉዳዩ የመንግስት ግዥና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ የበላይ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ፡-

- ኤጀንሲው በግዥ ሂደትና አፈፃፀም፣ ሙያዊና ተቋማዊ ስልጠና እንዲሁም ሀገራዊ የግዥ ስርዓቱ የተሻሻለ እንዲሆን ለማድረግ ለክልል መንግስታት፣ ለመንግስት የልማት ድርጅቶችና ለግሉ ዘርፍ በእቅድ ይዞ ስልጠና እና የማማከር አገልግሎት እየሰጠ እንደሚገኝ፣
- በተጨማሪም በመንግስት ግዥና ንብረት ማስወገድ አገልግሎት ላይ የሚታዩ ችግሮችን በመለየት ችግሮቹ የሚፈቱበትን አግባብ ከአገልግሎቱ ጋር በጋራ በመሆን አጀንዳ በመቅረፅ እንደሚወያዩ ገልፀዋል፡፡ ነገር ግን ከዚህ በፊት ጥር 2005 ዓ.ም በሁለቱ መካከል የነበረው የጋራ መግባቢያ ሰነድ እንዳልታደሰ/ወቅታዊ እንዳልተደረገ አክለው ገልጸዋል፡፡

199. የአገልግሎቱ የበላይ ሀላፊዎች የግዥ ስልጠና ተግባር በዕቅድ ይዞ ስልጠና መስጠት የግዥና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ ተግባር/ሀላፊነት በመሆኑ አገልግሎቱ ጥያቄ ሲቀርብለት ብቻ ስልጠና እንደሚሰጥ ቢገልፅም አገልግሎቱ በግዥ አፈጻጸም ዙሪያ የምክርና ስልጠና አገልግሎት መስጠት እንዳለበት በአገልግሎቱ ማቋቋሚያ ደንብ ላይ የተቀመጠ በመሆኑ የተሰጠውን ምላሽ ለመቀበል ያስቸግራል፡፡

ክፍል ሦስት

የመደምደሚያ ሀሳብ (Conclusion)

200. በአገልግሎቱ በጋራ የሚፈለጉ ተመሳሳይ ዕቃዎችና አገልግሎቶች የማዕቀፍ ስምምነት ግዥ አፈጻጸምና ውጤታማ መሆኑን ለማረጋገጥ ተከናውኖ በቀረበው የኦዲት ማሻሻያ ሀሳቦች የተወሰደ እርምት እርምጃ መኖሩን ለማረጋገጥ በተከናወነው የክትትል ኦዲት የሚከተሉት መሻሻሎችና እርምጃ ያልተወሰደባቸው ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡፡

እነርሱም፡-

3.1. እርምጃ የተወሰደባቸውና መሻሻል የታየባቸው

- በአገልግሎቱ የግዥ አፈፃፀም ሂደቱን የሚያሳዩ የግዥ ሰነዶችና ማስረጃዎች ማደራጃ ክፍል ያለው መሆኑና በተደራጀ ሁኔታ የተቀመጠ መሆኑ እና ለዚህም ክፍል የመረጃ ስራ አመራር ባለሙያ እና ሰነድ ያዥ ባለሙያ የተመደበ መሆኑ፤
- አገልግሎቱ የደንብ ልብሶች እና የኢንሹራንስ መድህን አገልግሎት ግዥ እየፈጸመ መሆኑ፤
- የፌዴራል ባለበጀት መስሪያ ቤቶች እና የመንግስት ዩኒቨርሲቲዎች ከውል ውጭ የሆነ የቅድመ ክፍያ የማይፈጽሙ መሆኑ፤
- አገልግሎቱ መ/ቤቶችንና ዩኒቨርሲቲዎችን የግዥ ፍላጎታቸው እስከ ሚያዚያ 30 ቀን እንዲልኩ የፍላጎት መጠየቂያ ከአንድ ወር በፊት የሚልክ መሆኑ፤
- አገልግሎቱ በመንግስት መ/ቤቶች በጋራ የሚፈለጉ ተመሳሳይ ዕቃዎችና አገልግሎቶች ግዥ ዙሪያ አልፎ አልፎ በሚዘጋጁ የውይይት መድረኮች ለባለድርሻ አካላት ግንዛቤ የማስጨበጥ ሥራ እያካሄደ መሆኑ፣
- በመንግስት ግዥና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲና በመንግስት ግዥና ንብረት ማስወገድ አገልግሎት የተፈጠረውን የስም መደበላለቅ ለማጥፋት በዓመት ሁለት ጊዜ በሚካሄዱ ለባለበጀት መ/ቤቶችና ለአቅራቢዎች በሚዘጋጅ የግንዛቤ ማስጨበጫ መድረክ ላይ ብሮሸሮችን በማዘጋጀት እንዲሰራጭ የተደረገ መሆኑ፣ እንዲሁም ለተለያዩ ሚዲያዎች ሰፊ ማብራሪያ መግለጫ የሚሰጥ መሆኑ፣

- አገልግሎቱ ግዥዎችን በአይነት፣ በመጠን፣ በጥራት ደረጃ እና በተለያየ ምድብ/ሎት/ የሚመድብና የሚያደራጅ መሆኑ፤
- አገልግሎቱ አመታዊ የግዥ እቅድ እና የእቅድ ክንውን ሪፖርት በማዘጋጀት ለኤጀንሲው የሚልክ መሆኑ፤
- አገልግሎቱ ከ10,000,000.00 ብር በላይ ዋጋ ያላቸው ግዥዎችን በዓለም ዓቀፍ ግልፅ ጨረታ እያከናወነ መሆኑ፤
- አገልግሎቱ በጋራ ለሚፈለጉ ዕቃዎችና አገልግሎቶች ግዥ የሚውል የጨረታ ሰነድ ለጨረታ ከማዋሉ በፊት በግዥ አፅዳቂ ኮሚቴ የሚፀድቅ መሆኑ፤
- አገልግሎቱ ለዕጩ ተጫራቾች የቅድመ ቴክኒክ እና የዝርዝር ቴክኒክ ግምገማ (preliminary & technical evaluation) የሚያካሂድ መሆኑና በቴክኒካል ግምገማ ወቅት የሁሉም ተጫራቾች የገቢና ወጪ ሂሳብ የሚያሳይ የባንክ ማስረጃ፣ አግባብነት ያለው የውል አፈጻጸም ስለመኖሩ የሶስተኛ ወገን ምስክርነት የሚገልጽ ማስረጃዎች የቅድመ ቴክኒክ ግምገማ እንደአስገዳጅነት መስፈርት በማድረግ በባለሙያዎች ተግባራዊ እየተደረገ መሆኑ፤
- አገልግሎቱ በቴክኒክ ግምገማ የሚወድቁ ዕቃ አቅራቢዎች ወደ ቀጣዩ የፋይናንስ ግምገማ እንዲያልፉ አለመደረጉ፤
- አገልግሎቱ የመንግስት መ/ቤቶች እቃውን ከተረከቡ በኋላ በውሉ መሰረት ከ5-10 ባሉት ቀናት ውስጥ ለአቅራቢ ድርጅቶች ክፍያ እንዲፈፅሙ ትእዛዝ የሚያስተላልፍ መሆኑና ትእዛዙን ተግባራዊ የማያደርጉ መ/ቤቶችን ለገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚ/ር የሚያሳውቅ መሆኑ፤
- አገልግሎቱ የግዥ ውሉ በስምምነቱ መሰረት ስለመፈጸሙ ከ2010 ዓ.ም ጀምሮ በተወሰነ መልኩ የደሰሳ ጥናት ያከናወነ መሆኑ ነገር ግን ከዚህ በፊት ለተደረጉት ግዥዎች ማለትም 2008ና 2009 ዓ.ም በውሉ መሰረት ስለመፈፀሙ ክትትል አለማድረጉ፤
- አገልግሎቱ የተጫራቾችን የውል ማስከበሪያ ገንዘብ በመከታተል የሚያሳድስ መሆኑ፤
- አገልግሎቱ ከኢትዮጵያ የተስማሚነት ምዘናና ከኢትዮጵያ መድህን ድርጅት ጋር የጋራ የስምምነት ሰነድ የተፈራረመ ቢሆንም ከሌሎች አጋር አካላት ጋር ቅንጅታዊ አሰራር ያልዘረጋ መሆኑ፤

- አገልግሎቱ ወደ ኢትዮጵያ የተስማሚነት ምዘና ድርጅት ለቅድመ ናሙና ፍተሻ የሚላኩት ዕቃዎች የጥቅም ግጭት እንዳይፈጥሩ የዕቃ አቅራቢውን የሚገልፅ ምልክት በማንሳት የናሙና ኮድ በመስጠት የሚያስፈትሽ መሆኑ፤

3.2. እርምጃ ያልተወሰደባቸው እና መሻሻል ያልታየባቸው

- አገልግሎቱ በደንቡ የተሰጠውን ኃላፊነት ለመወጣት የሚያስችሉ የግዥ ዳይሬክቶሬት እና የውል አስተዳደር ዳይሬክቶሬት በመዋቅሩ መሰረት የሰው ሀይል ያላሟላ መሆኑ፤
- አገልግሎቱ የተሽከርካሪ ግዥን በተመለከተ በራሱ ፍላጎት አሰባስቦ ግዥ የማይፈፅም መሆኑ፤
- አገልግሎቱ የተሽከርካሪ መለዋወጫዎች፣ የምግብ ጥሬ ዕቃዎች፣ መፅሐፍትና መፅሔቶችን በማዕቀፍ የማይገዛ መሆኑ፤
- አገልግሎቱ የህንፃ መሳሪያዎችና የግንባታ ዕቃዎችን በተመለከተ በማእቀፍ ግዥ መመሪያ መግዛት ሲገባው መመሪያውን በመጣስ በሌሎች የግዢ ዘዴ እየገዛ መሆኑ፤
- አገልግሎቱ የግዥ ዕቅዱን በግዥ አፈፃፀም መመሪያ አንቀጽ 12 (የግዥ ዕቅድ ይዘትን በተመለከተ) እና በዓመታዊ የግዥ ዕቅድ ማቅረቢያ ሠንጠረዥ አባሪ 1 መሰረት የግዥ ዕቅዱን ያላዘጋጀ መሆኑ፡፡
- አገልግሎቱ የግዥ ሂደቱን በቴክኖሎጂ የመጠቀም ስርዓትና ዘመናዊ የመረጃ አያያዝና ልውውጥ ተግባራዊነት በተጠናከረ መልኩ እየተገበረ አለመሆኑ፤
- አገልግሎቱ የሚያዘጋጀው የግዥ እቅድ ግምታዊ የበጀት መጠን ያላካተተ እንዲሁም የግዥው አይነት፤ ጨረታ የሚወጣበት ጊዜ፤ ግዥ ተፈፅሞ ርክክብ የሚፈፀምበት ጊዜ በተሟላ ሁኔታ ያላካተተ መሆኑ፤
- አገልግሎቱ ላለፉት ሶስት አመታት (ከ2008-2010 ዓ.ም) በተደረገው የግዥ ሂደት የነባር የዕቃና አገልግሎት አቅራቢ ድርጅቶች በጨረታ ወቅት በድጋሚ ለመወዳደር የበፊት የሥራ አፈጻጸማቸው እንደመስፈርት አለመታየቱ፤
- ለአገልግሎቱ በኤጀንሲው በጋራ መጠቀሚያ ዕቃዎች ዝርዝር ያካተታቸው ዕቃዎች (11 ምድብ) የተሰጠ ቢሆንም የሁሉንም ምድቦች ግዥ አለመፈጸሙ፤ እንዲሁም የፅዳት፣ የጥበቃና የጥገና አገልግሎት ግዥዎችን ያላከናወነ መሆኑ፤

- አገልግሎቱ ለፌዴራል መንግስት መ/ቤቶችና ዩኒቨርሲቲዎች በጀመረው የግዥ ሂደት የግዥ ትዕዛዝ ያስተላለፉበት ዕቃ በሚፈለገው መጠንና ጊዜ ተከታትሎ እንዲደርሳቸው አለማድረጉ፤

- የ2008-2010 ዓ.ም የግዥ ሂደቱ ተጠናቆ ውሉ የተገባው ከህዳር እስከ ግንቦት ባለው ጊዜ ውስጥ ማለትም ከሁለተኛው ሩብ እስከ አራተኛው ሩብ አመት በመሆኑ የመንግስት መ/ቤቶች የበጀት ዓመት/ፕሮግራም/ ታሳቢ ያላደረገ መሆኑ፤

- አገልግሎቱ ለተለያዩ የፌዴራል ባለበጀት መ/ቤቶች እና የመንግስት ዩኒቨርስቲዎች በመጠንና በጊዜ የማቅረብ ችግር እንዳለባቸው ቅሬታ የቀረበባቸው አቅራቢዎች የተለየ የመከልከያ መስፈርት ሳያዘጋጅ ለቀጣይ ግዥ ተሳታፊ መደረጋቸው፤

- አገልግሎቱ አቅራቢ ድርጅቶች በስምምነቱ መሰረት ተግባራዊ ካላደረጉ የውል ማስከበሪያ ገንዘብ የመውረሻ ስርዓት ቢኖረውም የመንግስት መ/ቤቶች ባለፉት ሶስት ዓመታት በውሉ መሰረት እንዳላስተናገዷቸው የሚገልፁ ቢሆንም አገልግሎቱ ይህንን በማረጋገጥ ገንዘቡን ያልወረሰ መሆኑ፤

- ከዚህ በፊት በኢትዮጵያ ደረጃዎች ኤጀንሲ ደረጃ እንዲወጣላቸው ከተላኩት ውስጥ አሁንም 132ቱ ዕቃዎች ደረጃ ተዘጋጅቶ ያልጸደቀላቸው መሆኑ፤

- አገልግሎቱ የተሽከርካሪ ጎማዎችን በሚመለከት ከአንበሳ አውቶብስ ድርጅት እንዲፈተሽ የጠየቀበት ሁኔታ ቢኖርም በመፈተሻ ማሽን እጥረት ምክንያት ፍተሻው አለመከናወኑና ይህን ፍተሻ ለማከናወን ሌላ አማራጭ ያልተጠቀመ መሆኑ፣ እንዲሁም በኢትዮጵያ የተስማሚነት ምዘና ድርጅት በመፈተሻ መሳሪያ እጥረት ምክንያት መፈተሽ ያልተቻሉትን እቃዎች እንደ ቶነር፣ ካርትሬጅና የመሳሰሉትን እቃዎች ከሌሎች አካላት መፈተሽ የሚቻልበትን ሁኔታ ያላመቻቸ መሆኑ፤

- አገልግሎቱ በየበጀት ዓመቱ በመ/ቤቶች ለሚፈለጉ የጋራ መጠቀሚያ ዕቃዎችና አገልግሎቶች የግዥ ገንዘብ ግምታዊ በጀት የሚመለከተውን አካል ስለማይጠይቅ ለግዥው የተመደበው በጀት እና የግዥው መጠን መመጣጠኑን እንደማያረጋግጥና ማስተካከያዎች የማያደርግ መሆኑ፤

- አገልግሎቱ የግዥ እቅዱን ለፌዴራል መንግስት መ/ቤቶችና ዩኒቨርሲቲዎች

የማያሳውቅ መሆኑ፤

- አገልግሎቱ የራሱን ዳታቤዝ ከመመስረት ባለፈ በቴክኖሎጂ የተደገፈ የመረጃ ልውውጥ ስርዓትን ተግባራዊ ያላደረገ መሆኑ፤
- ለመንግስት መ/ቤቶች ተመሳሳይ በጋራ የሚፈለጉ ዕቃዎችና አገልግሎቶች ጥቅል ግዢ በመፈፀም ያስገኘው የኢኮኖሚያዊ ጥቅም በገለልተኛ አካል አለመጠናቱ፤
- አገልግሎቱ በማዕቀፍ ግዥ አፈፃፀም ዙሪያ በራሱ እቅድ ይዞ የሰጠው ስልጠና አለመኖሩ፤

ክፍል አራት

<u>የማሻሻያ ሀሳቦች (Recommendation)</u>

201. በመጀመሪያው የክዋኔ ኦዲት ወቅት በተገኙ ግኝቶች ላይ የተሰጡት የማሻሻያ ሃሳቦች የተወሰኑት የእርምት እርምጃ የተወሰደባቸውና መሻሻል የታየባቸው ሁኔታዎች በመኖራቸው ተጠናክረው መቀጠል አለባቸው፡፡

202. ነገር ግን ከዚህ በፊት በተሰጠው የማሻሻያ ሀሳብ መሠረት ባልተስተካከሉና የእርምት እርምጃ ባልተወሰደባቸው የኦዲት ግኝቶች ላይ ከዚህ በፊት በተሰጠው የማሻሻያ ሀሳብ መሰረት አስፈለጊውን ክትትል በማድረግ የእርምት እርምጃ ሊወሰድ ይገባል፡፡

በመጨረሻም በክትትል ኦዲት ወቅት የመንግስት ግዥና ንብረት ማስወገድ አገልግሎት ኃላፊዎችና ሠራተኞች ላደረጉልን የሥራ ትብብር እናመሰግናለን፡፡